## ደቂቀ ነቢያት

የደኅርት ነቢያት ሁለተኛው ክፍለ ደቂቀ ነቢያት/ማይነር ፕሮፊትስ/ ናቸው። እነዚህም ከሆሴዕ እስከ ሚልክያስ ያሉት ናቸው። ደቂቅ መባላቸው መልእክታቸው በዐበይት ነቢያት መልእክት የሚያንስ ሆኖ አይደለም። በዘመነ መቀዳደም አይደለም። ነገር ግን በጽሑፋቸው ማጠር ብቻ ደቂቀ ወይም ንኡሳን ነቢያት ይባላሉ። ለምሳሌ ለደቂቀ ነቢያት ጠቅላላ ምዕራፎች 64 ቁጥሮቻቸውም 1060 ነው። ይህን ቁጥር በመጽሐፈ ኢሳይያስ ምዕራፍና ቁጥር ጋር ስናወዳድረው መጽሐፈ ኢሳይያስ በሁለት ምዕራፎች በ232 ቁጥሮች ይበልጣል። በዚህ አንጻር ሁሉም ደቂቀ ነቢያት ተጠቃልለው አንዱን የኢሳይያስ መጽሐፍ እያህሉም ማለት ነው። ከእነዚህም መካከል ትልቁ በአለ 14 ምዕራፍ ሲሆን ትንሹ ደግሞ በአለ አንድ ምዕራፍ ነው።

በዕበራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ደቂቀ ነቢያት " ዐሥራ ሁለቱ" ተብለው ይጠራሉ። እንደ አንድ መጽሐፍም /ጥቅልል/ ይቆጠራሉ። መጽሐፈ ሲራክ በምዕራፍ 49 ውስጥ ዐበይት ነቢያትን በስም በስማቸው እየጠራ ሲናገር መጥቶ ከሕዝቅኤል በኋላ የደቂቀ ነቢያትን ስሞቻቸውን ሳይዘረዝር "ዐሥራ ሁለቱ ነቢያት" በማለት ብቻ አጥፎ ጠቅልሎ ይናገራል /ሢራ.49÷10/ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንም አንድ መጽሐፍ አድርጎ ጠቅሶአቸዋል።

ዲቤላይም ብሎ ይጠራዋል። እንደገናም በምዕራፍ 5 ቁጥር 1 ላይ በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ምጽጻና ታቦር የተባሉ የቦታ ስሞች በግእዙ አይገኙም። ይህን የመሰለ ጥቃቅን ልዩነት በብዛት ሊገኝ ይችላል ይህም ልዩነት ሊመጣ የሚችለው መጽሐፉ ቅዱስ በየጊዜው ከቋንቋ በሚተርጉምበት ጊዜ መሆኑ የተረጋገጠ ነው። ከዚህ በላይ በተመለከትናቸው የዘርአ ልዩነቶች የአማርኛው እደ ዕብራይስጡ ነው። ግእዙ ግን ዕብራይስጡን አልተከተለም።

በምዕራፍ አከፋፈልም፡- በግእዙ የምዕራፉ 1 ቍጥሮች 11 ሲሆኑ በአማርኛው ግን 9 ቍጥሮች አሉት። ግእዙ ከምዕራፍ 2 ላይ ሁለት ቍጥሮች ወደ አንደኛው ምዕራፍ ጨምሮአል፡ በዚህ መሠረት ሁለተኛው መዕራፍ በግእዙ ባለ 24 ቍጥር ሲሆን በአማርኛው ደግሞ ባለ 25 ቍጥር ሆኖአል። እንደዚሁም በግእዙም ሆነ በአማርኛው የምዕራፍ 13 -16ኛው ቁጥር በዕብራይስጡ ምዕራፍ 14 መነሻ ነው። ስለዚህም በግዕዝና በአማርኛም ምዕራፍ 13 ባለ 16 ቁጥሮች ነው። በዕብራይስጡ ግን 15 ቍጥሮች ብቻ አሉት። ምዕራፍ 14 ደግሞ በግእዙና በአማርኛው ዘጠኝ ቍጥሮች ይገኙበታል። የዕብራይስጡ ግን 10 ቍጥሮቹን ይዞአል።

በግእዙ መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያው ላይ የሰብዓ ሊቃናትን ምዕራፍ አከፋፈል ተከትሎአል። በመጨረሻው ላይ ግን የዕብራይስጡን በመጨረሻውም የሰብዓ ሊቃናትን የምዕራፍ አከፋፈል ተከትሎአል። የምዕራፉ አከፋፈል ሥራ የመጀመሪያዎቹ ጸሐፍት ሥራ ላይሆን የኋላ ሰዎች ያዘጋጁት ስለሆነ እስካሁን ድረስ በተለያዩ ትርጉሞች ሁሉ አንዳንድ ልዩነት ይገኛል። ይሁን እንጂ ቃሉ የእግዚአብሔር በመሆኑ በልዩነት ምክንያት መጽሐፉ ስእተተኛ ነው አይባልም።

**አከፋፈሉ**

**ትንቢተ ሆሴዕ በሁለት ክፍሎች ይከፈላል።**

ሀ. ምዕራፍ 1፣1-3 ፣ 5 ዜማ የሆነችው የሆሴዕ ሚስት ታሪክና ምሳሌያዊ ትርጉም።

1. ምዕራፍ 1፣1 የመጽሐፉ ጠቅላላ መግቢያ ሲሆን ነቢዩ የነበረበትንም ዘመንያስረዳል። ቍጥር 2-9 ሆሴዕ ጎሜር የተባለች ሴት አግብቶ ሦስት ልጆችን መውለዱን ይተርካል። የጎሚር ጠባይና የZስቱ ልጆች ስም በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከለ ያለውን ግንኙነት ያመለክታል። ጎሜር ከሆሴዕ ጋር ከመጋባትዋ በፊትም ይሁን በኋላ አመንዝራ መሆንዋ የእስራኤልን ከእግዚአብሔር መለየትና ጣዖት

ማምለካቸውን ያሳያል የሆሼዕ የመጀመሪያ ልጅ ይዝራኤል ነው። ትርጉሙም እግዚአብሔር ይዘራል ማለት ነው። ይህም የእስራኤልን በምርኮ መበተን ያመለክታል። የሁለተኛዋ ልጅም ስምዋ ለረሩሃማ ነው። ትርጉሙም ምሕረት አልባ ማለት ነው ግእዙ ኢሣሕልት ይላታል። ምስጢሩም ቁ.6 ላይ ተገልጦአል። ሦስተኛው ልጅ ሎዓሚ ነው። ሕዝቤ አይደለም ማለት ነው። በግእዙ -ሕዝብየ ይለዋል። ይህም እስራኤል በኃጢአታቸው ከእግዚአብሔር ሕዝብነት እንደሚወጡ ያሳያል።

2. ምዕራፍ 2፣1-25 በምዕራፍ 1 የተተረከውን ታሪክ ይተረጉማል። አልፎ አልፎ ተስፋ አለበት። ለምሳሌ በክፉ የተተረጉመው ይዝራኤል በመልካም ተተርጉሞአል /ቁ.2/። ሉዓሚ፡- ዓሚ/ ኢ-ሕዝበየ ሕዝብየ /ሴፋሃማ፡- ሩሃማ/ ኢሣሕልት፡- ሥሕልት ተብሎ ተለውጦአል /ቁ-3/

3. ምዕ. 3፣ 1-5 ሆሴዕ ሚስቱ ከእርሱ ጋር የነበራትን ፍቅር ለውጣ ወደ ሌላ ከሄደች በኋላ መልሶ ይዋጃታል። ይህም ድርጊት የእስራኤልን ልጆች እግዚአብሔር በምሕረቱ እንደሚታረቃቸውና መልሶ ሕዝቡ እንደሚያደርጋቸው ያመለክታል። /ቁ.5/

ለ. ምዕራፍ 4፣1-14፣9 በካህናትና በሕዝቡ በቤተ ነጋሚውም ላይ የተደረገ ወቀሳ።

1. ምዕራፍ 4፣1-9፣9 ካህናት ከሕዝቡ ባለመሻላቸው ሕዝቡንም ካለመምከራቸውና ካለማስተማራቸው ሌላ ወደ ኃጢአት በመምራታቸው ይወቀሳሉ /4፣1-10/። ሕዝቡም እግዚአብሔርን ትተው በጣዖት በማምለካቸው /4፣11-19/። እንደገና ካህናቱም ሕዝቡም፣ መሪዎችም ተባብረው ኃጢአት በመሥራታቸው ይዘለፋሉ /5፣1-7/። ምዕራፍ 5፣8-6፣6 ሆሴዕ ምንም እንኳ ነቢዩ እስራኤል ቢሆንም ይሁዳንም ይወቅሳል። መልእክቱ ለሁሉ ነውና። ምዕራፍ 6፣7-9፣9 ነቢዩ ቤተ እስራኤልን በልዩ ኃጢአታቸው እየደጋገመ ይጠቅሳቸዋል።

2. ምዕራፊ 9፣10-13፣16፡- ሆሴህ 1- ለኃለኛው ኃጢአት መነሻ የሆነባቸውን ከግብጽ ሲወጡ በየቦታው ያደርጉትን የቀድሞውን ዐመጽ ሁሉ እያስታወሰ እስራኤልን ይገሥጻል።

3. ምዕራፍ 14፣ 1-9 እስራኤል ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ነቢዩ የእግዚአብሔርን ጥሪ ያስተላልፋል። ትንቢተ ሆሴዕ ምንም የወቀሳ ቃል ቢበዛበት መጀመሪያውም አስደንጋጭ ቢመስል መደምደሚያውም ምሕረት እግዚአብሔር በመሆኑ ለጊዜው ለቤተ እስራኤል ፍጻሜው ግን ለዓለም ሁሉ ተስፋ ደንንን ያበሥራል።

## ዘኢዩኤል

### ስሙ

ኢዩኤል ማለት እግዚአብሔር አምላክ ማለት ነው የቤተክርስቲያናችን የብሉይ ኪዳን ሊቀውንት ዘንረዮ እግዚአብሔር ንሩየ እግዚአብሔር ማለት ነው ብለው ይተረጉማሉ። መሠረተ ቃሉ ግን ይህን ትርጉም አያመለክትም። መጽሐፉ የተሰየመው በጻፈው በባቱኤል ልጅ በኢዩኤል ስም ነው። ስለ ኢዩኤል የሚናገር ከዚህ በቀር ሌላ የብሉይ ኪዳን ጽሑፍ አናገኝም። በሐዲስ ኪዳን ግን ቅዱስ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ 2፣16 ላይ እርሱ የተናገረውን ሲጠቅስ የኢዩኤልን ስም አንሥቶአል።

የኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ስለ ኢዩኤል ሲተርኩ "ትውልዱ ከነገደ• ሮቤል፣ ነው። አባቱ ባቱኤል፣ እናቱ መርሱስ ይባላል ይላሉ ስለ አባቱ በምዕራፈ 1፣1 ላይ ስለተገለጠ አከራካሪ አይሆንም። ነገር ግን ስለ ትውልዱና ስለ እናቱ የቀረበው ሃሳብ ምንጩ ባለመገለጡ ተቀባየነት ሊኖረው አይችልም።

### ነቢዩ ኡዮኤል ስለነበረበት ዘመን

አንዳንድ ዘመናውያን ሊቀውንተ ነቢዩ ኢዩኤል የነበረበት ዘመን ድንረ ፍልሰተ ባቢሎን በ4ኛው ምእተ ዓመት ቅልክ እንደሆነ ገምተዋል። ለዚህም የሚያቀርቡአቸው ማስረጃዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. አይሁድ በአሕዛብ መካከል እንደተበተኑ ተገልጦአል /ኢዩኤል 3፣2/
2. በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ ሕዝብ "እስራኤል" በሚለው በቀድሞ የአንድነት ስማቸው ተጠርተዋል። የተከፈለው የሰሜኑ መንግሥት ግን አልተጠቀሰም። /ኢዩኤል 3፣16-17/።

3. በመጽሐፉ ውስጥ ነገሥት ወይመ ንጉሣዊ ፍርድ ቤት አልተጠቀሰም። ካህናትና ሽማገሌዎች ብቻ የሕዝቡ መሪዎች ሆነው ተጠቅሰዋል /ኢዩኤል 1፣13-14/ 2፣16-17/።

4. በመቅደሱ የተለመደው የዘወትር አገልግሎት ይፈጸም ነበር። በሥርዓተ አምልኮት ከሁለተኛው መቅደስ ጀምሮ ይፈጸም የነበረው የመጠጥ ቁርባን ይታይ ነበር /ኢዩኤል 1፣9፣13። 2፣14/።

5. በዚህ ነቢየ ዘመነ የኢየሩሳሌም ግንብ ተገንብቶ ነበር /ኢዩኤል 2፣9/። ስለዚህ ነቢዩ ኢዩኤል ከነህምያ በኋላ የነበረ መሆን አለበት /ኢዩ.2፣9/።

6. የቀደሙትን ነቢያትን መጽሐፈ ጠቅሷል /ኢዩኤል 2፣28-32። ሕዝቅ 36፣26-28።39፣29/

7. በዚህ መጽሐፍ ግሪካውያን ተጠቅሰዋል /3፣6/ የግሪካውያን ኃይል የታወቀው ድኅረ ፍልሰተ ባቢሎን እንጂ ቅድመ ፍልሰተ ባቢሎን አለነበረም።

እስካሁን በቁጥር 1 እስከ 7 በተጠቀሱት ምክንያቶች ኢዩኤል ከዒዋዊ በኋላ ከተነሡት ነቢያት አንዱ ነበር የሚለውን አስተያየት ተመልክተን አሁን ደግሞ ኢዩኤል ቅድመ ዒዋዊ ከነበሩት ከመጀመሪያዎቹ ነቢያት አንዱ ነበር የሚሉትን የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት አስተያየት እንመለከታለን።

1. በመጽሐፈ ኡዩኤል የተጠቀሱት የይሁዳ ጠላቶች በምርኮ ጊዜ በፍልሰተ ባቢሎን ጊዜ የነበሩ ሶርያ አሶርና ባቢሎን ሳይሆኑ አሎፍላውያን እና ፊኒቃውያን /ኢዮ.3፣4/ ግብጽና ኤዶም /ኢዩ.3፣19/ ናቸው። በኢዩአሰ ዘመን /836-797/ ሶርያና አሦር በየሁዳ ላይ አደጋ ለመጣል ገና አልጀመሩም ነበር። ግብጽ ግን ቀደም ብላ ክሮብዓም ዘመነ መንግሥትም ጊዜ የይሁዳ ጠላት ነበረች። በኢዮራምም ዘመን /849-842/ ቅልክ ኤዶምና ኤሎፍሊ ከይሁደ ጋር ጦርነት ጀምረው ነበር /2ነገሥ.8፣2-22 ጊዜና 21፣16-17/

2. መጽሐፈ ኢዩኤል በሆሴዕና በአሞጽ መካከል መጠረዙ ራሱ በአይሁድ ትውፊት ጥንታዊነት መታመኑን ያመለክታል።

3. ከጥንታዊያን ነቢያት መካከል አንዱ በሆነው በአሞጽና በኢዩኤል መጻሕፍት መካከል አንዳንድ ግልጥ የሆነ የትንቢት አቀራረብ ንብረት ይገኛል።

ለምሳሌ፦ ኢዩኤል 1፣15ን ከአሞጽ 5፣18 ጋር፣ ኢዩአልን 3፣16ን ከአሞጽ 1፣2 ጋር እንደገናም ኢዩኤል 3፣18ን ከአሞጽ 9፣13 ጋር አነጻጽር።

**የመጽሐፉ ዓላማ**

የመጽሐፈ ኢዩኤል ዓላማ፦ የሚመጣውን ፍትሐ እግዚአብሔር በመግለጥ ሕዝቡ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ለማስጠንቀቅ ነው። በተጨማሪም የሚመጣውን ድኅነትን የጠላቶቻቸውን ድመሳሴ በማስታወስ እግዚአብሔር ለሚሰጠው ተስፋ የሕዝቡ ልብ አማኝ እንዲሆን ለማድረግ ነው። በኋለኛው ዘመን መንፈስ ቅድስ በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ እንደሚወርድ በግልጥ ይናገራል /ኢዩ.2፣28-32/

**አከፋፈሉ**

መጽሐፈ ኢዩኤል በሁለት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል።

ሀ. ምዕራፍ 1፣1-2፣27 የአንበጣ መቅሠፍት

1. 1፣1 የመጽሐፉ ርእስ ነው። ነቢዩ ኢዩኤል እንደሌሎች ነቢያት ያገለግለበት ሀገር ወይም ዘመን በመቅድሙ ላይ አልተገለጠም። በዚህም ምክንያት ነቢዩ ስለነበረበት ዘመን የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ከላይ እንደተመለከትነው ሁለት አስተያየቶችን ለመስጠት ችለዋል።

2. 1፣2-20 በመጽሐፉ በአንበጣ መቅሠፍት ምሳሌ የጀምርና /ሉ.2፣4/ ንስሐን ይሰብካል። ካህናቱ የእርድ ቀን ስለቀረበ በቤተ መቅደስ ጸምንና ገባኤን እንዲያውጅ ይታዘዛሉ /ሉ.5-14/

3. በምዕራፍ 2፣1-7 የጌታ ቀን ስለቀረበ መለከት እንዲነፉ ያዝዛል ይህን ጠላት ወደ ከተማዋ /ኢየሩሳሌም/ የሚገባበት የጨለማ /የወረራ/ ቀን ነው።

ከቁጥር 3-10 ኢዩኤል ስለዚህ ወረራ ሠራዊት ገለጣ ይሰጣል። እግዚአብሔር ከራሱ ሠራዊት ጋር ይህን ወራሪ ጠላት እንደሚገጥመው ያስታውቃል ቁ.11። ስለዚህ ሕዝቡ ንስሐ መግባት ጾም መጾም እንዳለባቸው ይናገራል። /ቁ.12-17/ እግዚአብሔር ሕዝቡን በንስሐ እንደሚያድናቸው የታመነ መሆኑን ይገልጣል።

## ለ. ምዕራፍ 2፣28-3፣21 የእግዚአብሔር በረከትና ፍርድ

በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍ ሁለት ቁጥር 27 ያልቃል።
ከቁጥር 28-32 ያሉ ቁጥሮች 3ኛ ምዕራፍ ናቸው። በግእዙ በአማርኛው ሦስተኛ ምዕራፍ የሆነው ክፍለ በዕብራይስጡ 4ኛ ምዕራፍ ነው። ስለዚህ የግእዙ 2፣28-32 የዕብራይስጡ 3፣1-5 ነው። የግእዙ /የአማርኛው /3፣1-21 የዕብራይስጡ 4፣1-21 ነው። የእኛ የግእዙም /የአማርኛውም/ ትርጉም ከሰብዓ ሊቃውንት የተተረጎመ መሆኑን በዚህ አከፋፈል ይታወቃል።

1. ምዕራፍ 2፣28-32 በመሢሑ ዘመን የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ እንደሚወርድና ወንጌል ለሁሉ እንደሚሰበክ የተነገረ ትንቢት ነው። የእግዚአብሔር ስመ የሚጠራ ሁሉ ይድናል። የዚህ ትንቢት መልእክት በበዓለ ሃምሳ ዕለት መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ ተፈጽሞአል። የሐዋ 2፣17።

2. 3፣1-21 በምሳሌያዊ ቋንቋ በመጠቀም ለሕዝቢ የበረከት ዘመን እንደሚመጣ ይተነብያለ የይሁዳና የኢየሩሳሌም ምርኮ እንደገና ይመለሳል ነገር ግን በአሕዛብ ላይ በቀላቱ ዮስፍጥ ፍርድ ይሆንባቸዋል /ቁ.1-8/ ለሕዝበ እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ በረከት ሲሆን በእነዚህ አሕዛብ ላየ ደግሞ የጦርነትና የፍርድ ዘመን ይሆናል።

መጽሐፈ ኢዩኤል በበረከት ይደመደማል "ይሁዳ ለዘለዓለም፡ ኢየሩሳሌም ለልጅ ልጅ መኖሪያ ይሆናል።

## ዘአሞጽ

አሞጽ ማለተ ሸክም ማለት ነው። ከኢሳይያስ አባት ከአሞጽ የተለየ ነው።

በዕብራይስጥ፡- የኢሳይያስ አባት አሞጽ ተብሎ ሲጠራ ይህ ነቢይ ግን አሞጽ ይባላል።

የኢትዮጵያ ሊቀውንት ግን፡- አሞጽ ማለት ጽኑእ በእግዚአብሔር ጽንእ እግዚአብሔር ጽኑእ እግዚአብሔር ማለት ነው ብለው ይተረጉማሉ። ለዚህም ማስረጃ ሲሰጡ አሞጽ ኤዜቅ እንዲል ይላሉ። ይሁን እንጂ ይህ ትጥስ ከየት እንደሚገኝ አልተገለጠም። በተጨማሪም አሞስ ይላል ይሉና ይህም ውጽድ ማለት ነው። ይባሉ። ትውልዱም ከነገደ ስመዖን እንደሆነ አባቱ ቴና፣ እናቱ ሚስታ ይባሉ እንደ ነበር ይተርካሉ።

ጸሐፊው

የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ራሱ ነቢዩ አሞጽ ነው። አሞጽ ከጸሐፊት ነቢያት መካከል መጀመሪያው ነው። በይሁደ ውስጥ በምትገኝ ቴቶ ሄቲቂሔ በተባለች አነስተኛ ከተማ ይሃረ ነበር። ቴሄ ከኢየሩሳሌም 15 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ከቤተልሔም በምሥራቅ ደቡብ በኩል ትገኛለች። አሞጽ ላም ጠባቂና 1፣1/ የዋርካ ፍሬ ለቃሚ /7፣14/ ነበር ነቢዩ በነበረበት ዘመን የዋርካ ፍሬ በእስራኤል አገር የድሆች ምግብ ነበር። አሞጽ በዕለታዊ ተግባሩ ተሠማርቶ ሳለ ለሰሜኑ ሕዝብ ነቢይ እንዲሆን እግዚአብሔር ጠራው /7፣14-15/ ይህም የሆነው በዳግማዊ ኢዩር ብዓም ዘመን 783-743 ነበር። ራሱ ነቢዩ የህን ጥሬ ሲያብራራ አንዲህ ይላል። እግዚአብሔርም በጎቼን ከመከተል ወሰደኝ እግዚአብሔርም ሂድ ለሕዝቤም ለእስራኤል ትንቢት ተናገር አለኝ።

አሞጽ ያስተማራቸው ሕዝብ ምን አይነት እንደነበሩ ከትንቢቱ ለመረዳት እንችላለን። ለምሳሌ፡- ባለጸጐች በራሳቸው የሚተማመኑና ክፉ ነገር እንደማይደርስባቸው ያረጋግጡ ነበር። ባለጸጐች ድሆችን ይጨቁኑ ነበር። ፍትሕ ርትዕ በአደባባዮቻቸው አይታይም ነበር ይህን በመመልከት ነቢዩ አሞጽ ክፉዎችን ገሠጻ ወደ እግዚአብሔርም እንዲመለሱ ለመናቸው።

**የመጽሐፉ ዓላማ**

ትንቢተ አሞጽ፡- እግዚአብሔር ለኃጥአን የሚያደርገውን ምሕረት ያስረዳል። የለሜኑ ሕዝብ እስራኤል ለዳዊት የተሰጠውን ቃል ኪዳንና ማንኛውንም የያህዌን ተስፋ ንቀው ነበር። በክንፈራቸው እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር። ልባቸው ግን ከእርሱ የራቀ ነበር። በሕይወታቸው ራስ ወዳድነት፣ ስስት፣ የሥነ ምግባር ጉድለት ድሆችን መጨቆን ይታይ ነበር።

በአገራቸው ፍትሕ አልነበረም። እንደ እነዚህ ያሉትን ሕዝብ ሊገሥጽ ሊያስተምርና ሊያስጠነቅቅ አሞጽ ተላከ።

መጽሐፉ አሥራውያንን አይጠቅስም ግን በእነርሱ ኃይል ስለሚሆነው ቄዋዊ አስቀድሞ ይናገራል። ከትንቢተ አሞጽ ዓላማዎች አንዱ ማስጠንቀቅ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ በክርስቶስ ስለሚሆነው ደኅንነት ተስፋ መስጠት ነው። ይህም፡- እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ባለው ታማኝነት የሕዝቡን ምርኮ በሚመልስበት ጊዜ አንደሚገለጥ በምዕራፍ 9፣11-15 ላይ ተገልጦአል።

## አከፋፈሉ

**ትንቢተ አሞጽ በአራት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል።**

ሀ. ምዕራፍ 1፣1-2፣16 በአሕዛብ ላይ የተነገረ ፍርድ

1. 1፣1ᵃየመጽሐፉ ርእስ ነው። አሞጽ የሚያስተምር ለስሜናዊው ሕዝብ መንግሥት/ ሆኖ ሳለ፡- በቅድሚያ የይሁዳን ንጉሥ ማንሳቱ እርሱ የሚቀበል የዳዊትን ዘርአ መንግሥት ብቻ መሆኑን ያመለክታል።/ ሆሳዕ 1፣1/ በዚህ ቍጥር የተጠቀሰው የመሬት መናወጥ፡- አሞጽ ትንቢት ከተናገረ ከ2 ዓመት በኋላ ግን ተንቢቱን /መልእክቱን/ ከመጻፉ በፊት የሆነ ነው። /ዘካ.14፣5/ ይህም የመሬት መናወጥ በ760 ዓመት ቅልክ በይሁዳ የደረሰው መናወጥ እንደሆነ ሊቃውንት ይገምታሉ።

2. 1፣2 እግዚአብሔር ከጽዮን ሆኖ ይናገራል ምክንያቱም ሕጋዊ መቅደስ ሃትና

3. 1፣3-2፣3 በስድስቱ አሕዛብ ላየ የነገረው ፍርድ 6ቱ አሕዛብ የተባሉት የሚከተሉት ናቸው። ደማስቆ /ሦርያ/ 1፣3-5። ፍልስጥኤም /ጋዛ/ 1፣6-8 ፊኒቄ/ጢሮስ/ 1፣9-10። ኤዶመ 1፣11-12። አሞን 1፣13-15። ሞዓብ 2፣1-3 የመጀመሪየዎቹ ሦስት ከእስራኤል ጋር የሥጋ ዝምድና የሌላቸው ሲሆኑ የመጨረሻዎቹ ሦስቱ ግን ዝምድና አላቸው ነቢዩ አሞጽ ደረጃ በደረጃ ወደ እስራኤል ይቀርባል።

4. 2፣4-16 በሕዝብ ወሬ ላይ የተነገሩ ትንቢቶች

ይሁዳ 2፣4-5 እስራኤል 2፣6-16 በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን የይሁዳንና የእስራኤልን ኃጢአት ብዛት ለመግለጥ ሰለ 3 ወይም ሰለ አራት ኃጢአታቸው መቀሠፍቱን ከማድረግ አልመለስም "የሚለውን የፍርድ ቃል ነቢዩ ይደጋግማል። ይህም የኃጢአታቸውን ብዛት ለመናገር እንጂ በሦስትና በአራት የተወሰነ ሆኖ አይደለም ዐሥር ጊዜ የተፈታተኑኝ /ዘኍል.14፣22/ እንዳለው ያለ አነጋገር ነው።

**ለ. ምዕራፍ 3፣1-6፣14 በእስራኤል የተነገረ ፍርድ**

1. 3፣1-15 እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር /በቱጣ/ በጸብ ቃል ይነጋገራል።
2. 4፣1-13 እስራኤል ባለፈው ቅጣት ወደ አግዚአብሔር አለመመለሳቸውን ይናገራል።
3. 5፣1-27 እግዚአብሔር ቤተ እስራኤልን በተዋረደች ድንግል መስሎ በሙሽ ይናገራል።
4. 6፣ 1-14 በእስራኤል ላይ የሚሆነውን ፍርድ ሁሉ በዋይታ ቃል ይገልጣል። የዚህ ምዕራፍ ይዘት ከምዕራፍ አምስት ጋር ተመሳሳይ ነው።

**ሐ. ምዕራፍ 7፣1-9፣10 የሚመጣውን ፍርድ የሚያመለክቱ አምስት ራእዮች**

1. 7፣1-3 መጀመሪያው ራእይ የአነበጣ መቅሠፍት ሲወርድ የታየ ነው።
2. 7፣4-6 እሳት ታላላቅ ምንጮችን ሁሉ ሲያደርቅ የታየ ነው።
3. 7፣ 7-17 ሦስተኛው ራእይ እስራኤል በቱንቢ ሲለካ የታየ ነው። በዚህ በሦስተኛው ራእይ ላይ የካህን ቤቴል የአሚሳያስ ተቃውሞና አሞጽ ከእስራኤል ወጥቶ ወደ ይሁደ እንዲሄድ የሰጠው ትአዛዝ ጣልቃ ገብቶአል። ይሁን እንጂ ተቃውሞው የተነሣ በራእዩ ምክንያት መሆኑ በቁጥር 12 ላይ ተገልጦአል። በዚህም ተቃውሞ ምክንያት አሞጽ ወደ አገሩ ይሁዳ ተመልሶ ትንቢቱን ጽፎአል።
4. 8፣1-14 አራተኛው ራእይ የቃርሚያ ፍሬ ስለሞላበት ዕንቅብ የታየ ራእይ ነው።
5. 9፣1-10 አምስተኛው ራእይ ስለቤተመቅደስ የታየ ራእይ ነው።

አራቱ ራእዮች ሁሉ "ጌታ እግዚአብሔር አሳየኝ በማለት የተነገሩ ሲሆኑ አምስተኛው ግን ጌታን አየሁት" በማለት ተነግሮአል ይሁን እንጂ ምሥጢሩ አንድ ነው። አሞጽ በመጀመሪያዎቹ በሁለቱ ራእዮች ጊዜ ጸሎት አደረገ። መቅሠፍቱም እንደማይሆን ጌታ አስታወቀው።

በሦስቱ ራእዮች ግን ነቢዩ አልጸለየም፣ መቅሠፍቱ የማይቀር ነውና።

መ. ምዕራፍ 9፣11-15 በመሢሑ ጊዜ ስለሚሆነው ተስፋ በረከት የነገረ ትንቢት

1. 9፣11 በመሚሉ ዘመን የማይፈጸመውን ተስፋ ያመለክታል። ይህም እንደተፈጸመ ለማስረዳት ያዕቁብ በሐዋርያት ሥራ 15፣16-18 ጠቅሶታል።

2. 9፣ 13-15 ተስፈ ማጣትን ያበሥራል። የአሞጽ ትንቢት በመጀመሪያ በሕዝብም በአሕዛብም ላይ የቅጣት ቃላትን/ የፍርድ ቃላትን/ ይናገራል። በመጨረሻችን ለሕዝቡም ለአሕዛቡም በሚሆን ታላቅ በረከት ይደመድማል። የመጽሐፉም ዋና መልእክት ይህ በመጨረሻው ክፍል የነገረው ትንቢት ነው። 9፣11-15

## ዘአብድዩ

### ስሙ

አብዳዩ ማለት ገብረ እግዚአብሔር ማለት ነው። በዕብራይስጡ አጠራር አባድያህ ይባላል። በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም አብድዩ ሲባል በዱልጋታ ደግሞ አብድያስ ተብሎ ይጠራል። የግእዙ መጽሐፈ ቅድስ ስም የሰብዓ ሊቀናት ይከተላል።

### ስለ ነቢዩና ስለ ነበረበት ዘመን

በስሙ የተሰየመውን መጽሐፈ ከመናገሩ በቀር ስለ አብጽዩ የሚታወቅ ሌላ ታሪክ የለም። ከዚህም የተነሣ"አብድዩ" ልዩ መጠሪያ ስም ሳይሆን ለማንመ የእግዚአብሔር ሰው የሰጠ ቅጽል ነው የሚሉ አሉ። ይሁን እንጂ በዚህ አስተያየት ብዙዎች የብሉይ ትንቢተ አብድዩ ብቻ ነው።

ነቢዩ የነበረበትና መጽሐፉ የተጻፈበት ዘመን በመጽሐፉ ላይ ተገልጠ አልተነገረም ነገር ግን ከ11-14 ባሉት ቁጥሮች ላይ የሰፈረውን ታሪክ በመመርመር ሁለት የተለያዩ አስተያየቶች በሊቃውንት ተሰጥተዋል።

1. ከ11-14 ባሉት ቁጥሮች የተገለጠው የኤዶምያስ ዓመጽ በኢዮራም ንጉሠ የሁዳ ዘመን የተደረገው ነው። ስለዚህም አብድዩ በኢፍሬም ዘመን /849-842/ ነበረ የሚሉ አሉ። ለዚህም የሚያቀርቡት ማስረጃ 2ኛ ዜና መዋዕል 21፣8-10። አሞጽ 1፣6 ነው። ይህ ከሆነ አብድዩ ከጻሕፍት ነቢያት አንዱ ነው። ለማለት እንችላለን።

2. ሌሎች ደግሞ በእነዚህ ቁጥሮች /11-14/ የተገለጠው ታሪክ ናቡከደነጾር በ586 ቅልክ ኢየሩሳሌምን ባጠፋ ጊዜ የተፈፀመ ታሪክ ነው። ነቢዩ አብድዩም የነበረ በዚሁ ዘመን ነው ይሉና የሚከተለውን ይጠቅሳሉ። መዝ.136፣7። ሰቆ.ኤር. 4፣21-22። ሕዝ.25፣12-14። 35፣1-9። ይህ ሁለተኛው አስተያየት በበዙዎች የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ዘንድ ተቀባይነት አለው። ምክንያቱም በዚሁ ዘመን በይሁዳ ትንቢት ይናገርና ያስተምር በነበረው በኤርምያስና በአብድዩ መካከል ስለ ኤርምያስ በይሁዳ ላይ ማመጽ ተመሳሳይ ቃል ይገኛልና። ለምሶሌ አብድዩ 1-9 እና ኤዶምየስ 49፣7-22 ያሉት መልእክቶች ምንም እንኳ ጥቃቅን ልዩነት ቢታይባቸውም ጠቅላላ ሀሳባቸው አንድ ነው። ከዚህም ላይ ሦስት አስተያየቶች አሉ።

1. አብድዩ በኢዮራም ዘመን ነበር የሚሉት ክፍሎች ከቁጥር 1-9 ስለ ኤዶምያስ የተነገረውን ተግሣጽ በመጀመሪያ አብድዩ ከተናገረው በኋላ ኤርምያስ እንደ ጥቅስ አድርጎ ወስዶታል ይላሉ።

2. ሌሎች ደግሞ በመጀመሪያ የተናገረው ኤርምያስ ነው። አብድዩ ከኤርምያስ ጠቅሶታል ይላሉ። እንደዚህም የሚሉት አብድዩ በ460 ቅልክ እንደነበረ የሚገምቱ ዘመናውየነ የብሉይ ኩዳን ሊቃውንት ናቸው።

3. አብድዩና ኤርመያስ በአንድ ዘመን ስለነበሩ በኤዶምያስ ላይ ስለሚሆነው አንድ ዓይነት ፍርድ በተመሳሳየ ቃል ተናገሩ የማሉ አሉ። በብዙዎቱ ሊቃውነቱ ዘንድ የሚደገፈውመ ይህ ሦስተኛውም አስተየየት ነው። የኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንትም በዚህ ይስማማሉ።

ኤዶምያስ በሙት ባሕር /ባሕረ ዔው/ ደቡብ የምትገኝ፣ ጥቂት ሕዝቦች የሚኖሩበት ሀገር ነበረች። በሀገሪቱ የኖሩት የነበሩ የዔሣው ዘሮች ናቸው ትንቢተ አብድዩ በጠቅላላ የሚያመለክተው ይችን ትንሽ ሀገር ነው። በመጨረሻ ግን ከቁጥር 17-21 የእስራኤላውያንን፣ በተለይም በጽዮን የሚኖሩትን ሕዝብ ተስፋ ይናገራል።

### የመጽሐፉ ዓላማ

ትንቢተ አብድዩ፡- የኤዶምያስን በይሁዳ ላይ ማመጽ፣ ትዕቢትዋን፣ እንደገናም ማዋረድዋን ይገልጣል። ቀጥሎም ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ቀን ይናገራል። ይህም ለጊዜው ኤዶምያስ በኃጢአትዋ የምትቀጣበት ቀን ነው። ፍጻሜው ግን የመጨረሻውን የፍርድ ቀን ያመለክታል። በመጨረሻም ደኅንነትም ለእስራኤል፣ መንግሥትም ለእግዚአብሔር እንደሚሆን ያስረዳል።

### አከፋፈል

1. ቍጥር 1-9 የኤዶም ትዕቢት መውደቅ፣
2. ቍጥር 10-14 የኤዶምያስ ትዕቢት ምክንያት ኢየሩሳሌም በመውደቅዋ ኤዶምያስ ተደስታ ነበር።
3. ቍጥር 15-21 በአሕዛብ ላይ የእግዚአብሔር ቀን ለፍርድ እንደሚመጣ የእግዚአብሔር ተስፋ መንግሥት በይሁዳ እንደሚመሠረት ይናገራል።

ማስታወሻ፣ ትንቢተ አብድዩ ከደቂቀ ነቢያት መካከል ባለአንድ ምዕራፍ በመሆኑ ከእርሱ ጥቂት በምንጠቅስበት ጊዜ ወይም በምናነብበት ጊዜ ቍጥር ብቻ እንጂ ምዕራፍ አንጠቅስም። ይህም በመጽሐፈ ቅዱስ ውስጥ አንድ ምዕራፍ ባላቸው ሁሉ ላየ የተለመደ ሥርዓተ ንባብ ነው። ለምሳሌ ከፊልሞና ከሁለተኛና ሦስተኛ ዮሐንስ እንዲሁም ዮሐንስ እንዲሁም ከይሁዳ መልእክታት ስንጠቅስ ቍጥር ብቻ እናስቀምጣለን እንጂ ምዕራፍ አንድ አንልም። አንደኛ ማለት የሚቻለው ሁለተኛ ሲኖር ነው። በዚህ አንጻር ቍጥር ስንጠቅስ ሁለተኛ ብቻ ከሆነ አንድ ሁለት እንላለን። ግን ከአንድ እስከ ሁለት አንልም።

## ዘ ዮናስ

### ስሙ

ዮናስ ማለት ርግብ ማለት ነው። በዕብራይስጡ አጠራር ዮናህ ነው። በስብዓ ሊቃናት ግን ዮናስ የሚለውን መልክ ይዞአል። በላቲኑም ጆናስ ይባላል። የግእዙም ትርጉም የሰብዓ ሊቃናትን ተከትሎአል።

## ስለ ነቢዩ ዮናስና ስለነበረበት ዘመን

ዮናስ በገሊላ ውስጥ የምትገኘው የጋትሔፈር ሰው የአማቴ አሚቴ/ ልጅ ነው። በቤተክርስቲያናችን የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ስለዮናስ የሚከተለው ታሪክ ይተርካል።ወሀሎ አሐዱ ወልደ ብእሲት ዘሰራጵታ "ዮናስ በሰራጵታ ትኖር የነበረችው መበለት ልጅ ነው። በሕጻንነቱ ሞተ ኤልያስ አስነሣው። የኤልያስም ደቀ መዝሙር ሆኖ አደገ /1 ነገሥ. 17፣17-23/ ከእርሱ ጋር ሳለ ሀብተ ትንቢት ተሰጠቱት ነበር ይህ ታሪክ ነቢዩ ዮናስ ከቀደምት ነቢያት አንዱ መሆኑን ያረጋግጣል ግን ወደፊት ለምንመለከተው ታሪክ ተስማሚ መስሎ አይታይም።

በብሉይ ኪዳን፡- ከራሱ ትንቢት ውጭ በ2ኛ ነገሥት 14፣25 ላይ ብቻ ስለ ዮናስ ተጠቅሶአል። ይሁን እንጂ በዚህ ጥቅስ ላይ ዮናስ የተናገረው ቃል ምን እንደሆነ በዝርዝር አልተገለጠም። ግን ከዚህ ጥቅስ ላይ ዮናስ በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመን /783-743/ ቅልክ ለነቢይነት ተጠረቶ ብቻ እንደነበረ እንረዳለን። በዚህም ምክንያት ዮናስ ከመጀመሪያዎቹ የሥነ ጽሑፍ ነቢያት አንዱ እንደሆነ ለመረዳት እንችላለን።

ዮናስ በአክአብ ዘመን /876-854 ቅልክ/ የነበረው የኤልያስ ደቀ መዝሙር ከሆነ በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመን ሽማግሌ የሆናል። ስለዚህ የሰራጵታዊት ልጅ መሆኑ ትክክለኛ ታሪክ አይመስልም።

ነቢዩ ዮናስ ትንቢት የተናገረው በአሦራውያን ዋና ከተማ በነነዌ ነበር። ነነዌ በዛሬው ጊዜ ሞስል ተብላ ትጠራለች። ዮናስ በነነዌ ያስተማረው በራብዓዊ ስልምናሶር ዘመን/781-772/ ነበር ከትውልድ ሀገሩ ወጥቶ በአሕዛብ ሀገር የእግዚአብሔርን ቃል የሰበከ ነቢይ ዮናስ ብቻ ነው።

ትንቢተ ዮናስ መች እንደተጻፈ በመጽሐፉ ላይ ባይጠቀስም እንኳ ዮናስ ከነነዌ ከተመለሰ በኋላ ትነቢቱን እንደጻፈ ብዙዎች የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ይስማማሉ። የጽሕፉ ዓይነት የታሪኩ አቀራረብ በ3ኛ መደብ /በጆግራፊ/ በመሆኑ ጸሐፊው ዮናስ ላይሆን የዮናስን ትንቢት ሌላ ሰው እንደጻፈው የሚገምቱ ሊቃውንትም አሉ። ነገር ግን ዮናስ ለመጻፉ ወይመ ላለመጻፉ ከመጽሐፉ ውስጥ በቂ ማስረጃ እስካልተገኘ ድረስ የቀደመውን ተውፊት እንከተላለን።

**የመጽሐፉ ዓላማ**

ትንቢተ ዮናስ ከእስራኤል ወደ አሕዛብ የተላከ የብሉይ ኪዳን መልእክት እንደመሆኑ ለአሕዛብ የሆነውን የአግዚአብሔርን ፍቅር ይገልጣል። 4፣11/ መልእክቱ ለአይሁድ የማይስተዋል አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ነቢዩ ከእነርሱ አልፎ ወደ አሕዛብ ተልኮአልና። የመጽሐፉ ጠባይ ከሌሎች ነቢያት መጻሐፈት የተለየ ነው። ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የራሱን የነቢዩን የሕይወት ታሪክ ይናገራልና።

ዮናስ ስለ መሢሕ በቀጥታ የተናገረው ትንቢት ባይኖርም፡- በነቢዩ ላይ የተፈጸመው ተአምራዊ ታሪክ የመሢሑ ምሳሌ ነው። ዮናስ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በከርሠ አንበሪ ማደሩ፡- ማሢሕ 3 መዐልትና 3 ሌሊት በከርሠ መቃብር ማደሩን ያመለክታል። ማቴ.12፣39-41 ሉቃ. 11፣29-30/። ከነቢያት መካከል ለከረሰቶስ ምሳሌ ሆኖ በቀጥታ የተጠቀሰ ዮናስ ብቻ ነው። ወደ አሕዛብ የሆነው የዮናስ ተልእኮ የመሢሕ ተልእኮና አድነኖት ለእስራኤል ብቻ ሳይሆን ለአሕዛብም መሆኑን ያመለክታል።

**አከፋፈሉ**

**መጽሐፈ ዮናስ በ5 ይከፈላል።**

1. ምዕራፍ 1፣1-3 ለዮናስ የተሰጠው ትእዛዝና ዮናስ ከእግዚአብሔር የሆነውን ትእዛዝ ማቃለሉ።
2. ምዕራፍ 1፣ 4-17 የዮናስ ወደ ተርሴስ በመርከብ ላየ ሆኖ መኰብለልና የእግዚአብሔር ክትትል።
3. ምዕራፈ 2፣1-10 ዮናስ በከርሠ አነበሪ ሆኖ የጸለየው ጸሎት /መዝሙር/
4. ምዕራፍ 3፣1-9 የእግዚአብሔር ትእዛዝ ለዮናስ እንደገና መታደሉ
5. ምዕ3፣ 10-4፣11 በእግዚአብሔር ምሕረት የዮናስ አለመደሰትና የእግዚአብሔር ተግሣጽ

**ዘሚከያስ**

**ስሙ**

በዕብራይስጡ አጠራር ማክያህ /ሚካህ/ ወይም ሚካያሁ ይባላል፣ ትርጉሙም መኑ ከመ አምላክ ማለት ነው። በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ሚክያስ የሚል መልክ ይዞአል። የግእዙ

መጽሐፈ ቅዱስም ትርጉም፣ የሰብዓ ሊቃናትን በመከተል ሚክያስ ይላል። ስያሜው ከሚክያስ 7፣18 ላየ የተወሰደ ይመስላል።

ጸሐፊው

በሚክያስ የተሰየመው መጽሐፈ ተንቢት በጠቅላላ በምሬታዊው ነቢይ ሚክያስ የተነገረና የተጻፈ ነው። ሚክያስ የምሬት ሰው /ሞሬሸት ነው። ሞሬሽት በፍልስኤም የምትገኘው የጌት አነስተኛ ከተማ ነበረች። ስለዚህም አንዳንድ ጊዜ መምሬሽን ጌት እየተባለች ትጠራለች /ሚክ.1፣14/ ይህ ሚክያስ ከይምላ ልጅ ሚክያስ የተለየ ነው።/1ነገሥ.22፣8፣13-28/

ዘመኑ

የሚኪያስ የነቢይነት አገልግሎት ዘመኑ፣ በኢዩአታም በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመን ነበር በዚህ አንጻር ሚኪያስ የኢሳይያስ የዘመን ጓደኛ እንደ ነበር ለመረዳት እንችላለን። ይሁን እንጂ በመልእክት አቀራረባቸው ልዩነት ይታያል። ይህም ሊሆን የቸለው ኢሳይያስ በዋናው ከተማ በኢየሩሳሌም ይኖር ስለነበር መልእክቱ ወደ ባለሥልጣኖች ነበር። ሚክያስ ደግሞ በገጠር ለለኖረ መልእክቱ አካባቢውን ይመለከታል። እርግጥ በትክክል የሚገናኙበት ቃል አለ። ለምሳለ ሚክያስ 4፣1-5 እና ኢሳይየስ 2፣2-4 አነጻጽር።

ሚክያስ፡- በንጉሥ ሕዝቅያስ ዘመን የተናገራቸውን የትንቢት ቃላት/ሚክ.3፣12/ ነቢዩ ኤርምያስ /26፣18/ ከእነርሱም ጠቅሶ ተናግሮአል። በዚህም፡- ሚክያስ የነበረበትን ዘመን በተጨማሪ ከማረጋገጣችን በላይ የሚክያስን ታዋቂነትና የትመሀርቱን ተቀባይነት እንረዳለን።

**የመጽሐፉ ዓላማ**

የሚክያስ መጽሐፈ ብዙ ጊዜ ማስጠንቀቂያን የተመላ ነው። አልፎ አልፎም ስለ ተስፋ የተነገረ ትንቢት ይገኝበታል። ፍልሰተ ባቢሎንን ይናገራል /4፣10 የአሶራዊያንን ውድቀት /609-594/ ቅልክ ይገልጣል /5፣5-6/። መኳንንቱን፣ ካህናቱንና ነቢያተ ሐሰትን ይገሥጻል። /3፣5-12። 7፣3/። ድሆችን የሚጨቁኑ ባለጸጐችን አታላይ ነጋዴዎችን ይወቅሳል። /2፣1-2። 6፣10-11/ በዘመኑ በቤተ ሰብአ መካከል የነበረውን አለመተማመን በመግለጥ አንዱ ከሌላው መጠበቅ እንዳለበት ያስጠነቅቃለ /7፣5-6/ ስለ አምልኮትም ሥነ ሥርዓት፡- ሕዝቡ ፍቅር ርኅራኄ ትሕትና፣ መታዘዝ ሳይኖራቸው ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ትልቅ ስጦታ ሁሉ

በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባየነት እንደሌለው በማስረዳት በዚህ ፈንታ ሊያቀርቡት የሚገባቸውን ይናገራል /6፣6-8/።

ሚክያስ ስለመሢሑ መምጣትና ስለ አድነኖቱ በግልጥ ይናገራል። ነቢዩ ኢሳይያስ፡- ክርስቶስ ከማን እንደሚወለድ ገልጦ እንደተናገረ ሚክያስ ደግሞ በየት እንደሚወልድ ገልጦ ያስረዳል/5፣2-4/

**አከፋፈሉ**

ትንቢተ ሚክያስን በ3 ዓበይት ክፍሎች መክፈል ይቻላል።

ሀ. ምዕራፍ 1፣1-2፣13 እስራኤልንና የሁዳን የሚመለከቱ ትንቢቶች

1. 1፣1 የመጽሐፉ መቅድም ነው። የመቅድሙ ቃል የራሱ የነቢዩ ሳይሆን ቃለ ጸሐፊ ይመስላለ የሚሉ ሊቃውንተ አሉ። ይሁን እንደ በብዙዎች ነቢያት መጽሐፈ መቅድም ላይ ይህን የሚመስል ቀል ስለሚገኝ ባፅድ ያስገባው ቃል ሳይሆን የራሱ የሚክያስ ቃል ከመሆኑ አይወጣም።

2. 1፣2-16 በእነዚህ ቁጥሮች፡- በሰማርየና በየሁዳ ላይ የእግዚአብሐር ቁጣ ተገልጠአል። ሁለቱም ሰማርያና ይሁዳ ክፉት አድርገዋል፣ እግዚአብሔርመ ሁለቱን ለመቅጣት አቅዷል። ሚክያስ በዚህ ምዕራፍ ስለ ጥፊት የሚሰጠው ማብራሪያ በ722 ቅልክ በሰማርያ ላይ የሚሆነውን ውድቅት ብቻ ሳይሆን ጠቅላ የሕዝቡን ሞራላዊ ውድቀትንም ያመለክታል።

3. 2፣1-13፡- እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ደስተኛ ያልሆነባቸው ምክንያቶች 2፣1-11 የሕዝቡን ምልዓተ ኃጢአትና የእግዚአብሔርን የቅጣት ዓላማ ይገልጣል። በ12 እና በ13 ቁጥሮች ላይ ደግሞ ትንቢታዊ የድኅንነት ብሥራት ተመልክቶአል። ይህመ በመሢሕ ዘመን የሚሆነውን ደኅንነት ያሳያል።

**ለ. ምዕራፍ 3፡1-5፣15 ፍትሕና ደኅንነ ት**

1. 3፣1-12 ነቢዩበድጋሚ የሕዝቡን ኃጢአተኛነት፣ የገለጠበት፣ የኢየሩሳሌምን የመጨረሻ ውድቀት /ቁ.12/ የተናገረበት፣ ሁለተኛ ዐዋጅ ነው። ሁለተኛነቱመ በምዕራፍ 1 ቁ.2 ላየ "ስሙ" ለሚለው ዐዋጅ ነው።

2. 4፣1-5፣1 የእግዚአብሔር መንግሥት መቋቋም 1-3 በእነዚህ ቊጥሮች ላይ ያለው ትንቢት ከኢሳይያስ 2፣2-4 ካለው ጋር ይመሰላል። በመጀመሪያ ማን እንደተናገረው አልታወቀም። ግን አንዳንዱ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት በቅድሚያ ኢሳይያስ ተናግሮት በኋላ ሚክያስ እንደጠቀሰው ያምናሉ። የሁን እንጂ ከኢሳይያስ ይልቅ የሚክያስ ይመስላል። ምክንያቱም ከተከታታይ ቊጥሮች ጋር ግንኙነት አለውና። እንደዚሁም ማክ. 4፣3ን ከኢዩኤል 3፣10፣4፣7ን ኢሳ. 24፣23 ጋር፣ 4፣9ን ከኢሳ.13፣8 እና 21 ጋር ፣ 4፣13 ሆነ ከኢሳ.41፣15-16 ጋር 4፣13 ለን ከኢሳ.23፣18 ጋር አነጻጽር።

3. 5፣2-15 የመሢሕ ልደትና መንግሥት በቊጥር ሁለት ላይ ወደፊት የማመጣው የመሢሑውን ንጉሥ ልደት ተነግሮአል። ነቢዩ በዚህ ክፍለ የመሢሑን የልደት ቦታ ከመግለጡም በላይ ቀዳማዊነቱንና ዘለዓለማዊነቱን በጉልህ ያስረዳል። /5፣5ን ከኢሳ.9፣6 ጋር 5፣13ን ክኢሳ.2፣8 ጋር አነጻጽር።

**ሐ. ምዕራፍ 6፣1-7፣20 የሕዝቡ ቅጣትና የእግዚአብሔር ፍጽም ምሕረት**

1. 6፣1-16 እግዚአብሔር ሕዝቡን ይወቅሳል። በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ለሕዝቡ ብዙ ድንቅ ነገር እንደአደረገላቸው ተገልጦአል። ሕዝቡ ግን የተደረላቸውን ሁሉ በመዘንጋት ዓመጸኞች ሆነዋል። ሰለዚህ የእግዚአብሔር ሀሳብ በክርክር መልክ ቀርቦአል። የክርክሩም መልስ እግዚአብሔር ታዛቻቦነትንና ትሕትናን ብቻ እንደሚፈለግ መሆኑ ተገልጦአል።

   6፣2ን ከሆሴዕ 4፣1 እና 12፣2 ጋር 6፣4ን ከአሞጽ 2፣10 ጋር 6፣7ን ከኢሳ.1፣11 ጋር 6፣8ን ከኢሳ.7፣17 ጋር እና ከሆሴዕ 6፣6 ጋር፣ 6፣11ን ከሆሴ 12፣7 ጋር 6፣14ን በሆሴዕ 4፣10 ጋር አነጻጽር። ይህ ንጽጽር በአንድ ዘመን የተነገሩ የትንቢቶች ኅብረት ያመለክታል።

2. 7፣1-20 እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠውን ተስፋ እንደሚፈጽም የተነገረ ማረጋገጫ ቃል፣

/7፣1ን ከኢሳ.24፣13 እና ከሆሴዕ 9፣10 ጋር፣ 7፣2ን ከኢሳ.57፣1ጋር፣ 7፣3ን ከኢሳ.1፣23 ከሆሴዕ 4፣18 ጋር፣ 7፣10ን ከኢዮኤል 2፣17 ጋር፣ 7፣11ን ከአሞጽ 9፣11ጋር አነጻጽር/

## ዘናሆም

### ስሙ

ናሆም ማለት ዕረፍት /መጽናት/ ማለተ ነው በኢሳይያስ 57፣18 ላይ በአማርኛው መጽናናት የሚለው ቀል በዕብራይስጡ ናሆም ይባላል በግእዝ ቋንቋ ናህየ የሚለው ቃል ከዚህ ጋር የስማማል። በስብዓ ሊቃውንተ ትርጉም ናኡም የሚል መልእክት ይዘአል።

የቤተክርስቲያናችን የብሉይ ኪዳን ሊቃውነት ናሆም ማለት ፈውስ ፈውሰ አግዚአብሔር ማለት ነው ብለው ይተረጉማሉ። እናቱም ሳስና እንደምትባል ይተርካሉ።

### ጸሐፊው

በስሙ የተሰየመውን መጽሐፍ የጻፈ የኤልቆሽ ሰው ናሆም ነው። አሁን ኤልቆሽ የተባለው ቦታ በየት እንደነበረ እርግጠኛው አልታወቀም። ከዚህም የተነሣ የተለያዩ ሊቃውንት የተለየየ አስተያየተ አቀርበዋል።

1. ኤልቆሽ ሞሴል /ነነዌ/ አጠገበ የምትገኘው ኤለቊሽ እንደሆነች የገመቱ አንዳንድ ሊቃውንት አሉ።
2. በአይሁድ ውስጥ ያለችው ኤልቀሲ ናት ያሉም አለ።
3. ሄሮኒሞስ /ጀሮመ/ ግን በገሊላ የምትገኘው ኤልቃስሽ ቅፍርናሆም ናት ብሎአል። ይህም ትክክለ ይመስላል ምክንያቱም ቅፍርናሆም ማለት ሰፈረ ናሆም ማለት ነውና።

### ነቢዩ የነበረበት ዘመን

ትንቢተ ናሆም የነነዌን ውድቀት ይናገራል። ውድቀትምዋ ፈጥኖ እንደሚሆን የስረዳል። ይህ አነጋገር ነቢዩ ናሆም ከነነዌ ውድቀት /612/ ቅልክ ጥቂት ቀደም ብሎ በትንቢት አገልግሎት ላይ እንደነበረ ያስረዳል። እንደገናም ትንቢተ ናሆም በአሦራዊው ንጉሥ በአሹርባኒፖል የተፈጸመውን /የተደተረወን/ የኖአምንን መማረክ የጠቅሳል /3፣8/ ይህ ምርኮ

የሆነው በ664-663 ቅልክ ነበር። ስለዚህ ትንቢተ ናሆም የተነገረበት ዘመን በእነዚህ በሁለቱ ታሪኮች መካከል እንደነበረ ልንገምት እንችላለን።

ሌላም አስተያየት አለ፡- ኢዮስያስ በ621 ትልክ ሃይማኖታዊ ተሐድሶ ካተደረገ በኋላ ጥቂት ቆይቶ ናሆም እንደተነሣ 1፣15 ላይ የለው ጥቅስ ያመለክታል። በዚህም መሠረት ነቢዩ ናሆም በ621 እና በ612 መካከል እንደ ነበረ እንመለከታለን። ይህም ከሆነ ናሆም የሶፎንያስ የዕንባቆምና በኤርምያስ የዘመን ጓደኛ ነበር ለማለት እንችላለን።

## የመጽሐፉ ዓላማ

ትንቢተ ናሆም፡- ነነዌ ምንም ታላቅ ከተማ ብትሆን አሦርም ገናና መንግሥት ቢሆን በእግዚአብሔር ኃይል እንዳልነበሩ እንደሚሆኑ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ያረጋግጣል። ይህም ይፈጸም ዘንድ ነነዌ ለ2500 ዓመታት ያህል በአሸዋ ተቀብራ ፍራሽዋ እንኳ ሳይታወቅ ኖራለች። እንደዚሁም፡- እግዚአብሔር ፈጥኖ የማይፈርድ ትእግሥተኛ መሆኑን ይናገራል /1፣3/

አከፋፈሉ

ትንቢተ ናሆም በ3 ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል።

ሀ. ምዕራፍ 1፣1-15 እግዚአብሔር ለተቃዋሚዎቹ

መስተበቅል ለሚየምኑበት ግን መስተዓግሥና መስተሣህል /መሐሪ/ መሆኑን ያሳያል።

1. 1፣1 የመጽሐፍ ርእስ ነው
2. 1፣2-8 በቅኔ መልክ የተነገረ የእግዚአብሔር በቀል ነው። በመሠረቱ ምዕራፉ 2 በዕብራውያን አልፋ ቤት በቅኒ ግጥም መልክ የተዘጋጀ ነበር። ነገር ግን መጽሐፉ በየጊዜው ሲተረጎም ከጊዜ ብዛት የተነሣ የቅኔ መልኩ ጠፍቷል።
3. 1፣9-15 የተቃዋሚዎቹ የአሦራውያንን የቅጣት ፈርድና ለይሁዳ የተነገረውን አጽናኝ የተስፋ ቃል ይናገራል።

ለ. ምዕራፍ 2፣1-13 በ3 ዓይነት ድርጊት የተፈጸመ ቅጣት

1. ምዕራፍ 2፣1-6 ወረራ፣
2. ምዕራፍ 2፣7-10 ዘፈፋ
3. ምዕራፍ 2፣11-13 የመንግሥት ነነዌ ግፍታኤ /ውድቀት/

## ዘእንባቆም

### ስሙ

ስሙ በዕብራይስጥ ሀባቀቂት ይባላል። ሰብአ ሊቃናት እምባቆም በግእዝም እንባቆም ተብሎ ይጠራል። የስሙ ትርጓሜ በትክክለ በባይታወቅም የብሉየ ኪዳን ሊቃውንት የሚከተለውን ፍች ሰጥተዋል። "ሀባት" ማቀፍ ከሚል የዕብራይስጥ ግሥ ጋር በማዛመድ ሀባቂት ማለት ዕቅፍ ማለት ነው። ብለው የተረጎሙ አሉ። ሌሎችም ደግሞ ሀምባቂት ከሚባል በአሦር ከሚገኝ የተክል ሰም ጋር አገናዝበው የስሙ ተርጓሜ ተክል፣ ማለት ነው በለው ተርጉመዋል።

የኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንትም፡- እንባቆም ማለት ጠቢብ፣ ማእምር ወለብዊ ማለት ነው በለው ይተረጉማሉ። ይሁን እንጂ የቃሉ ትክክለኛ ፍች ዕቅፍ /ሕቁፍ/ ማለት ነው በንል ስህተት አይሆንም። ምክንያቱም ሀባቅ የሚለው ቃል ሀሳቊቅ ከሚለው የዕብራይስጥ ስያሜ ጋር ይቀራረባልና። የነቢዩም ትክክለኛ ስም እንደ አይሁድ አጠራር ሀባቊቅ ነው።

ስለ ነቢዩ እንባቆም ሀገርና፣ ትውልድ ዘመንም በራሱ መጽሐፍ ውስጥ ምንም አልተገለጠም። ነገር ግን በሰብዓ ሊቃናት ትውፊት "እንባቆም ወልደ ኢያሱ ዘእምነገደ ሌዊ እንባቆም ከሌዊ ወገን የኢያሱ ልጅ ነው። የሚል ታሪክ አለ። ከዚህም ሌላ ዳንኤል በባቢሎን ተማርካ ሳለ ለአጫጆች ምሳ ይዞ ሲሄድ የእግዚአብሔር መልአክ በራሱ ጠጉር አንጠልጥሎ ወደ ባቢሎን ወስዶ ለዳንኤል ምግብ እንዳቀበለው በዜና ቤል ወደ ራገን ተተርኮአል። /ዳንኤል 12፣32-38/ በትልቁ መ.ቅ. ተመልክተ / በዚህ ታሪክ መሠረት አንባቆም ከደገኛው ዔዋዊ /586 ቅልክ/ በፊት እንደነበረ ለመረዳት እንችላለን።

ከቅኖናውያን ነቢያት መካከል በራሱ መጽሐፉ ውስጥ ራሱን ነቢይ ብሎ የጠራ እንባቆም ብቻ ነው። /1፣1/ ይህም ነቢይነት በልዩ ጥሬ የሚገኝ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ከነቢያት ትምህርት ቤት የወጡም ነቢያት የሚባሉ መሆናቸውን ያሳያል። በአሞጽ 7፣14 ጋር አመዛዝን።

እንባቆም መቼ እንደነበረ በመጽሐፉ ላይ አልተገለጠም። ሆኖም በምዕራፍ 1፣6 "ከለዳውያንን አስነሣለሁ ስለሚል ከለዳውያን /ባቢሎናውያን/ ኃያላን በተነሡበት በ605 ዓመት

ቀልክ ገደማ ትንቢቱን መናገሩ ግልጥ ነው። አንዳንድ ሉቃውንትም ከኢዮስያስ ጥጻሚ ዘመነ መንግሥት /640-609/ እስከ ኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት /609-598/ ኖሯል ሲሉ ተርከዋል። ይህም ሀሳብ በ605 ዓመት ነበረ ከማለው ሀሳብ ልዩነት አይኖረውምና ተቀባይነት አለው።

የመጽሐፉ ዓላማ

ትንቢተ እንባቶም እግዚአብሔር ክፉት ሲበዛ ቢታገሥ፣ ክፉውችንም ለጊዜው መሣሪያ መሆኑን ያስረዳል።

አከፋፈሉ

**ትንቢተ እንባቆም በ3 ይከፈላል።**

ሀ. ምዕራፍ 1፣1-2፡4 የእንባቆም ጥያቄና የእግዚአብሔር መልስ

1. 1፣1-4 ክፋት እየበዛ ሲሄድ እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላይ? /የእንባቆመ ተሰእሎ ነው/ ተሰጥዎ ነው/ ከኡሳይያስ 10፣5-11 ጋር አነጻጽር
2. 1፣5-11 እግዚአብሔር ከለዳውያንን በማስነሣት ክፉወተን ይቀጣል /የእግዚአብሔር ተሰጥዎ ነው/ ከኡሳይያስ 10፣5-11 ጋር አነጻጽር
3. 1፣12-17 እግዚአብሔር ቅዱስ ከሆነ በርኩስ መሣሪያ ለምን ይጠቀማል? /የእንባቆም / ጠያቄ ተሰእሎ ነው።
4. ምዕራፍ 2፣1-4 ክፉ ሰው በክፋቱና በተዕቢቱ ይጠፋለ ጻድቅ ግን በእምነት በሕይወት ይኖራል። /የእግዚአብሔር መልስ ተሰጥዎ/ ነው።

ለ. ምዕራፍ 2፣5-20 አምስት የወዬታ ቃላት

1. 2፣5-8 የሌላውን ለሚቀማ ወዬለት
2. 2፣9-11 ክፉ ትርፍ ለሚሰበሰቡ ወዬለት
3. 2፣12-14 ከተማን በደም ለሚሠራ ወዬለት
4. 2፣15-17 ለሰካራምና ለአመንዝራ ወዬለት
5. 2፣18-20 ጣዖትን ለሚያመልኩ ወዬለት

ሐ. ምዕራፊ 3፣1-19 የእንባቆም ጸሎት መዝሙር

እግዚአብሔርም ቀደም ተገልጦአል፣ ለወደፊትመ ይገለጣል። ሰገለጥመ በአሕዛብ ላየ ይፈረዳል። ለሕዝቡም ድኅነትን ይሰጣል። በ1947/ እ.ኤ.አ/ የተገኘው የቁምራን ትርጓሜ ይህን

ሦስተኛ ምዕራፍ አይጽፍመ ይህንንመ መሠረት በማድረግ የእንባቆም ትንቢት ቀድሞ ባለ ሁለተ መዕራፍ ብቻ እንደነበረ የገመቱ ሊቃውንት አሉ። ይሁን እንጂ የመገመሩ ይዘት ከሁለት ምዕራፎች ጋር ተመሳሳይነት ስላለው፡- በኋላ የተጨመረ ሳይሆን ከመጀመሪያም የእንባቆም ነው።

## ዘሶፎንያስ

### ስሙ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዚህ ስም የተሰየሙ ሌሎች ሦስት ሰዎች አሉ። /1ዜና 6፣36-38። ኤር. 21፣1 ዘካ.6፣10/። የስሙ አጠራር በዕብራይስጥ ጼፋንያህ ነው። ትርጓሜው ሰውር/ከደኖ/ እግዚአ ማለት ነው የኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ግን ሰፋኒ፣ ቀዳሲ፣ ስሉጥ ማለት ነው ብለው ያትታሉ ነገር ግን ይህ ትርጓሜውም ከዕብራየስጡ ጋር አይስማማም። ሶፎንያስ የሚለው አጠራር የሰብዓ ሊቃናት ነው። ግእዙም ሆነ አማርኛው ይህንኑ ተከትሎአል።

### ስለ ጸሐፊው

በራሱ ስም የተሰየመውን መጽሐፉ የጻፈ ራሱ ሶፎንያስ መሆኑ ከጥንት ጀምሮ የታመነ ነው። ሶፎንያስ የነበረው በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት /640-609/ ቅልክ ነው። /1፣1/ ይሁን እንጂ ትንቢቱን የተናገረው ኢዮስያስ ካደረገው ሃይማኖታዊ ተሐድሶ ጥቂት ቀደም ብሎ ሳይሆን አይቀርም። ይህንም ከምዕራፍ 1፣4-6፣8-9፣12። 3፣1-3፣7 ላይ ለመረዳት እንችላለን ምክንያቱም በእነዚህ ቊጥሮች እንደተገለጠው የሕዝቡ ሃይማኖታዊና ሞራላዊ ጠባይህ ዝቅተኛ ነበርና። በኢዮስያስ ተሐድሶ ግን እነዚህ የተጠቀሱት የሞራል ውድቀቶች ሁሉ ተወግደው ነበር።

ሶፎንያስ ትውልዱን ለማስረዳት እስከ አራት ቤት ቆጥሮአል። በትውልዱ ውስጥ የተጠቀሰው ሕዝቅያስ ንጉሡ ሕዝቅያስ ከሆነ የንጉሣዊ ቤት ሰብአ ዘርአ መሆኑን ለማስረዳት ይሆናል፣ ነገር ግን የሶፎንያስ ቅድመ አያት የሆነው ሕዝቅያስ ንጉሡ ሕዝቅያስ ለመሆኑ ማስረጃ የለም። አንደንድ ሊቃውንተ ሶፎንያስ ወልደ ኩሲ የሚለውን ንባብ ይዘው ነቢዩ ሶፎንያስ ጥቊር ያውም ኢትዮጵያዊ እንደ ነበረ ገመተዋል። የኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ግን ትውልዱ ከነገደ ንፍታሌም ነው። እናቱም ንህባ ትባላለች በማለት ይተርካሉ።

ይህ ከሆነ ቅድመ አያቱ ሕዝቅያስ ንጉሡ አለመሆኑ ግለጥ ነው። ምክንያቱም የንጉሡ ሕዝቅያስ ትውልድ ከነገደ ይሁዳ ነውና።

የመጽሐፉ ዓላማ

የትንቢተ ሶፎንያስ ዓላማ፡- ክፉ አድራጊዎች ሕዝቡን ማስጠንቀቅ ነው። ስለ እግዚአብሔር የቍጣ ቀን ማለት ስለ ዔዋዊ ይናገራል። እንደ ገናም ስለሚጠትና በሚጠት ጊዜ የሚሆነው ነጻነት ይናገራል። በሚጠትም አንጻር የመሚሐን ዘመነ ያሳያል።

አከፋፈሉ

የሶፎንያስ ትንቢት በ3 ዐበይት ክፍሎች ልንከፍለው እንችላለን።

ሀ. ምዕራፍ 1፣1-2፣3 ዕለተ እግዚአብሔር

1. 1፣1 ጠቅላላ የመጽሐፉ ርእስ ነው። ከዚህ ቍጥር ላይ ሶፎንያስ የነበረበትን ዘመን ለመረዳት እንችላለን። ይኸውም በኢዮስያስ ዘመን ቃለ እግዚአብሔር መጣላት ስለሚል ነው።
2. 1፣2-6 እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከገጸ ምድር ያጠፋል። ይህም ጥፋት ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን፣ በእነርሱም የሚገኘውን ሰውን፣ አራዊትን፣ አዕዋፍን፣ የጣያትን አይነት ሁሉ ዘርአ መንግሥትንም ይመለከታል።
3. 1፣7-2፣3 ከ2-6 ባሉት ቍጥሮች ከተገለጠው ቅጣት በኋላ ዕለት እግዚአብሔር እንደቀረበ ነቢዩ ያውጃል። ይህ አሳፋሪና አስደንጋጭ የተባለው ዕለት እግዚአብሔር ለጊዜው የሦስቱን የዔዋዊ ዘመናት ያመለክታል ፍጻሜው ግን የመጨረሻው ፍርድ ቀን ነው። ምዕራፍ 2፣1-3 ሕዝቡ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ቢመለሱ እርሱንም ቢፈልጉ በቍጣው ቀን ምሕረት የሚደረግላቸው መሆኑን ያሳያል።

ለ. ምዕራፈ 2፣4-15 አሕዛብን የሚመለከቱ ትንቢቶች

ከዚህ ላይ ሶፎንያስ እንደሌሎች ነቢያት ሁሉ ወደ ጎረቤት አሕዛብ ወይም አረማውያን የተኩራል። ይህም ስለ ኃጢአታቸው ሊያስጠነቅቃቸው የእግዚአብሔር ቍጣ ባደረሰባቸው ጊዜ የኃጢአታችን ተፈረደብን እንደይሉ ምክንያት ሊያሰጣቸው እንደዚሁም፣ የእግዚአብሔር ኀሩያን ሕዝቡን የሚያሰቃዩትን የሚቀጣቸው መሆኑን ሊገልጥላቸው ነው።

ሶፎንያስ በመጀመሪያ በጋዛና በፍልስኤም ላይ /ቁ.4-7/ ይናገራል ቀጥሎም ሞዓብና አሞን የእስራኤል ጠላቶች ስለሆኑ /ቁ.8-11/ ያወግዛል። በመጨረሻም በኢትዮጵያ በሦርያና በነነዌ ላይ ጥፋት እንደማመጣባቸው /በቁ.12-15/ ይናገራል።

ሐ. ምዕራፍ 3፣1-20 የኢየሩሳሌም ኃጢአትና መጻኤው ነጻነትዋ /ሚጠት/

1. 3፣1-7 በኢየሩሳሌም ላይ ወዬታን ያውጃል ኃጢአትዋንም ይዘረዝራል
2. 3፣8-20 በሚጠት ጊዜ የሚፈጸመውን ነገር ይናገራል። ይኸውም ትሩፋ ፋራሊ እግዚአብሔር ይሆናል ለጽዮን ፍፁም ደስታ ይሆንላታል እግዚአብሔር በመካከልዋ ይሆናልና።

ሶፎንያስ በቁጣ ጀምሮ በመሕረት ይደመድማል። ይህም ዘለዓለማዊውን የእግዚአብሔር ፍቅር ያሳያል።

## ዘሐጌ

### ስሙ

ሐጌ ማለት በዓላዊ፣ በዓልየ፣ ዘተወልደ በዕለት በዐለ ማለት ነው በዓልን ተመልክቶ ስም ማውጣትም በአይሁድ ዘንድ የተለመደ ነው። ለምሳሌ ሰባታይ ዘተወልደ በዕለተ ሰንበት ማለት ነው። /ዕዝራ. 10፣15/ ሐግያህ / 1ዜና. 6፣30/ በዓለ እግዚኦ ማለት ነው። የቤተክርስቲያናችን የብሉይ ኪዳን ሊቃውንተ ግን ሐጌ ማለት መልአከ እግዚአብሔር ማለት ነው ይላሉ። ይህን ማለታቸው። ... ወይቤ ሐጌ መልአከ እግዚአብሔር ... ያለውን ንባብ ተመልክተው ነው። ይህ ንባብ ቅጽል እንጂ የቃሉ ፍች አይደለም። የስሙ አጠራር በሰብዓ ሊቃናት ትርጓሜ አጋይዮስ የሚል መልክ ይዞአል። ግእዙ ግን የዕብራይስጡን አጠራር ተከትሎአል።

### ስለ ጸሐፊው

በስሙ የተሰየመውን መጽሐፍ የጻፈ ራሱ ነቢዩ ሐጌ ነው። ነቢዩ ሐጌ በፀዋዌ ጊዜ በባቢሎን የተለደ ነው። በ536 ቅልቅ ንጉሥ ቂሮስ ትእዛዝ መጀመሪያ ከተመለሱት ዔውዋን ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሷል። /ዕዝ.1፣1-4። በዚያ ዘመን የተመለሱት ዔዋውያን የቤተ መቅደስን መሠረት ጀመሩ። መሠረቱ ከተጣለ በኋላ በተቃውሞ ምክንያት ሥራው ተቋረጠ /ዕዝ.4፣23-34/። ለ16 ዓመታት ያህል ሕዝቡ የራሳቸውን ቤት ሲሠሩ ቆዩ በ520 ቅልክ ሐጌና ዘካርያስ ተነሥተው ለ16 ዓመታት የተቋረጠው የእግዚአብሔር ቤት ሥራ እንዲቀጥል

የእግዚአብሔርን መልእክተ አስተላለፉ ሐጌና ዘካሪያስ የዘሩባቤልና የካህኑ ኢያሱ ረዳቶች ነቢያት ነበሩ /ዕዝ.5፣1 እና 6፣14/ ነቢዩ ሐጌ ካህን እንደነበረ የጥንት ቤተክርስቲያን ትውፊት አለ። ይህ አስተሳሰብ የተመሠረተው በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ በሐጌና በዘካርያስ ስም የተሰየመ መዝሙር /145-148/ ስለማግኘ ነው። ይህም ሐጌ በክህነት አገልግሎት ጊዜ የዘመረው መዝሙር ነው ለማለት ነው።

**የመጸሐፉ ዓላማ**

ትንቢተ ሐጌ ሕዝቡ የተጀመረውን ቤተ እግዚአብሔር እንዲሠሩ ያበረታታል ለእግዚአብሔር ሊያደርጉት የሚገባቸውን ሳያስቀድሙ የራሳቸውን ቢሠሩ በረከተ እግዚአብሔር ማግኘት እንደማይችሉ የስጠነቅቃል።

**አከፋፈሉ**

ትንቢተ ሐጌ በአራት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል። አራት መልእክታት ይገኙበታልና።

1. 1፣1-15 1ኛ መልእክት፡- ይህ መልእክት በንጉሡ ዳርዮስ ቀዳማዊ በሁለተኛው ዓመት መንግሥት በስድስተኛው ወር /መስከረም/ በመጀመሪያው ቀን የተነገረ ነው። ሐጌ ይህን መልእክት ያስተላለፈው ለገዥው ለዘሩባቤልና ለሊቀ ካህናቱ ለኢያሱ /ዩሴዕ/ ወልደ አዩሴዴቅ ነበር/ ይሁን እንጂ መልእክቱ የሕዝቡን አስተሳሰብ ይመለከታል። ሕዝቡ፡- ቤተ መቅደስን ለመሥራት ጊዜው ገና ነው ብለው የራሳቸውን ቤት ያደራጁ ነበርና ነቢዩ ይህን ይቃወማል /1፣6/። ቤተ መቅደሱንም ለመሥር ያነቃቃቸዋል። በዚህ አስቸኳይ መልእክት መሠረት ሕዝቡና መሪዎች እግዚአብሔርን ፈሩ መልእክቱ ከተላለፈላቸው ከ23 ቀናት በኋላ በ24ኛው ቀን ቸል ብለውት የነበረውን የቤተ መቅደሱን ሥራ እንደገና ጀመሩ።
2. 2፣1-9 ሁለተኛው ቃለ መልእክት

   ይህ መልእክት በዚያው ዓመት በሰባተኛው ወር ከወሩም በ21 ኛው ቀን ተነግሮአል። ብዚ ማጸናናትንና ተስፋን የተሞላ መልእክት ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ ሽማግሌች ናቡከደነጾር በ586 ቅልክ ያፈረሰው የሰሎሞን ቤተ መቅደስ በክብር የበልጣል እያሉ በማሰብ የሠራተኞችን ልብ ማዳከም ጀምረው ነበር። ቢሆንም ነቢዩ ሐጌ፡- ከፊተኛው ይልቅ የዚህ የሁለተኛው ቤተ ክብር ይበልጣል፡- በዚህ ሥፍራ ሰላምን እሰጣለሁ ይላል

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር "በማለት የጽናናቸዋል። /2፣9/ በዚህ ክፍል የተነገረው የተስፋ ቀል ሁሉ በመሢሑ ጊዜ የሚፈጸመውን ተስፋ ያሳያል።

3. ምዕራፍ፣10-19 ሦስተኛው ቃለ መልእክት

ይህኛውም መልእክት በዚያው ዓመት በዘጠነኛው ወር በ24ኛው ቀን ሁለተኛው መልእክት በተላለፈ በሁለተኛው ወር የተነገረ ነው። በዚህ ክፍል ሐጌ "የተቀደሰው ነገር ርኩሱን አይቀድስም። ርኩስ ግን የተቀደሰውን ያስረክሳል"ይላል። ይህም ማለት ሕዝቡ ወደ ቀድሞው ቤተ መቅደስ የሚያደርጉት ልዩ አሰተሳሰብ የአዲሱን በተ መቅደስ ሥራ ያዳክማል፣ የእግዚአብሔርንም በረከት ያስቀራል። ማለት ነው። ግእዙ ግን የተቀደሰው ነገር ርኩሱን ቢነካ "ይትቄደስ ርኩስ" ይቀደሳል ይላል። ይሁን እንጂ ዕብራይስጡ እንደዚህ ስለማይል ግእዙ ትክክለ አይመስልም።

ነቢየ ሐጌ ይህን መልእክት ካስተላለፈበት ቀን ጀምሮ ህዝቡ ወደፊት ቢያስቡ የእግዚአብሔር በረከት የሚተረፈረፍላገርው መሆኑን ያበሥራል /2፣18-19/

4. ምዕራፍ 2፣20-23 አራተኛ ቃለ መልእክት

አራተኛው መልእክት በዚያው ቀን የተነገረ ሁለተኛ መልእክት ነው። መልእክቱ ለዘሩባቤል የተሰጠውን የተስፋ ቀል ይናገራል። ለዘሩባቤልም የተነገረው ተስፋ ትንቢት በዘመኑ አልተፈጸመም። ግን በመሢሑ ተፈጽሞአል። ዘሩባቤል የከረሰቶስ ምሳሌ ነው /ማቴ.1፣13/።

## ዘዘካርያስ ነቢይ

### ስለ ጸሐፊው

በዕብራይስጥ ዘካርያስ ይባላል። ትርጓሜው ዝኩር እግዚአብሔር ማለት ነው። በስብዓ ሊቃናት ትርጓሜ ዘካርያስ የሚለውን ስያሜ ይሏል ግእዙም ይህን የሰባ ሊቃናት አጠራር ተከትሏል። ዘካርያስ የሚለውም በእስራኤላውያን ዘንድ በተለምዶ ነው። ከዚህም የተነሣ በመጸሐፈ ቅድስ ውስጥ በዚህ ስም የተጠሩ 33 የህል ሰዎች ይገኛሉ። /ኢንተርፕሪተር ባይብል ዲክሽነሪ 4ኛ ቅጽ ዘካርያስ ተመልከት

ዘካርያስ የበራክዬ ልጅ የአዶ የልጅ ልጅ ነው /1፣1-7 በመጽሐፈ ዕዝራ 5፣1 ላይና ም዗.6፣14 ላየ ግን የአዶ ልጅ ተብሎአል። አንድ ሰው አንድ ጊዜ በአባቱ በሌላመ ጊዜ በአያቱ ስም ቢጠራ ልዩነትን አያመጣም ይህ አዶ በ1ኛ ዜና 27፣21 በ2ኛ ዜና 9፣29 ፣ 12፣15፣13፣22 አዶ በሚል ስም ከተጠቀሱት ሰዎች የተለየነው የነቢዩ አባት አዶ በዘሩባቤል ጊዜ ከባቢሎን ወደ ኡየሩሳሌም ከሌዋውያን ጋር የተመለሰው ነው። /ነህ.12፣1-4/ ዘካርያስም በዚያው ጊዜ ከሌዋውያን ጋር ተመልሰዋል /ነህ.12፣16/ በዚህ መሠረት ዘካርያስ በትውልዱ ከነደ ለዊ ከመሆኑም በላይ ካህንም ነቢይም እንደነበረ ለመረዳት እንችላለን።

የዘካርያስ አያት አዶ በሚጠት ጊዜ በሕይወት ከኖረ የልጅ ልጅ ዘካርያስ ወጣት ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም /ዘካ.2፣4/ ዘካርያስ ተልእኮውን የጀመረ ሐጌ ከጀመረ ሁለተ ወር ቆይቶ ነው። ስለዚህም ዘካርያስ የሐጌ የዘመን ጓደኛ ነበር/ ዕዝ.5፣12/ መዝ.145-148 አረእስት በትንቢተ ኢሳይያስ 8፣2 ላይ የተጠቀሰው ዘካርያስና ይህ ዘካርያስ ምንም እንኳ የሁለቱ አባቶች በራክዬ ተብለው በ2ኛው ትርጉም የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ቢጠሩ የተለያዩ ናቸው። የነቢዩ ዘካርያስ አባት በራክዩ ሲሆን የዚያኛው ግን ይቤራክዮ /ይቤራክያህ/ ነው። የጥንቱን መጽሐፍ ቅዱስ ተመልከት/ በዚህ ብቻ ሣይሆን የዘመን ልዩነትም አለ። በማቴዎስ 23፣35 በቤተ መቅደስና በመሠዊያው ላይ የተገደለው የበራክዩ ልጅ የተባለው ዘካርያስም ነቢዩ ዘካርያስ ሳይሆን በ2 ዜና መዋዕል 24፣20-22 ላይ የተገለጠው ዘካርያስ ወልደ ዬዳሄ ነው። ይህንም ለማረጋገጥ ሉቃስ ወልደ ብራክዩ አይለውም /ሉቃ.11፣51/

**ዘካርያስ በነቢይነት አገልግሎት የነበረበት ዘመን**

ዘካርያስ በቀዳማዊ ዳርዮስ በ2ኛ ዐመተ መንግሥቱ /520 ቅልክ/ የነቢይነት ተልእኮውን ጀመረ። /1፣1። በዱርዬስ 4ኛ ዓመተ መንግሥቱ /518 ቅልክ/ የነቢይነት አገልግሎቱን ፈጸመ 7፣1 በዚህ አንጻር የሁለተኛውን ቤተመቅደስ የሥራ ፍጻሜ አላየም የቤተመቅደሱ ሥራ ያለቀ በ516 ቅለክ ነውና ስለ መጽሐፉ በተነቢተ ዘካርያስ 1-8 ያሉ ምዕራፎች የነቢዩ ዘካርያስ ለመሆናቸው በውስጣቸው በቂ ማስረጃዎችን እናገኛለን። ከ9-14 የሉ ምዕራፎች ግን ከመጀመሪያዎቹ የለዩ ናቸው። የሀሳብና የአጻጻፍ ልዩነትመ ይታይባቸዋል በ6 ምዕራፎች ውስጥ የነቢዩ ስመ ፈጽሞ አልተጠቀሰም። ትንቢቶች የተነገሩበት ጊዜ እንደ መጀመሪያዎቹ አልተገለጠም። በዘካርያስ ዘመን ኃያላን የነበሩት ፋሪሳውያን እነ ዳርዮስ በእነዚህ 6 ምዕራፍች አልተጠቀሱም። በመጀመሪዎቹ 8 ምዕራፎች የተጠሩ መሪዎች ዘሩባቤልና ታላቁ ካህን ኢያሱ

አልተጠሩም በተለይም በመጀመሪያ የያዘው የቤተመቅደሱ ጉዳይ ፈጽሞ አልተነገረም። ስለዚህ እነዚህ 6 ምዕራፎች በነቢዩ ዘካርያስ የተጻፉ አይደሉም የሚሉ ሊቃውንት አሉ።

ከ9-14 ባሉት 6 ምዕራፎች ሁለት አረዕስት አሉ። ይኸውም የእግዚአብሔር ቃል ሸክም የሚለው ነው 9፣1። 12፣1 በአማርኛው የእግዚአብሔር ቃል ሸክም የሚለውን ዕብራይስጡ ማሣእ "ይለዋል። ተርጓሚውም /ዘተነሥአ/ የተሰደ ማለት ነው። ይህም ስድስቱ ምዕራፎች ከሌላ የተወሰዱ መሆናቸውን ያሳያል። ግእዙ ግን ተረፈ ቃል እግዚአብሔር ይላል ሀሳቡ ከላይኛው ጋር ይስማማል። ዘካርያስ 11፣12-13 በማቴዎስ 27፣9 እና 10 ላይ ተጠቅሶ ይገኛል። ይሁን እንጂ ወንጌላዊው ሲጠቀስ በዘካርያስ የተባለው ይፈጸም ዘንድ ሳይል "በኤርምያስ የተባለው ይፈጸም ዘንድ በማለት ጽፎአል። ይህን ሀሳብ በመከተል ከ9-11 ያሉ ምዕራፎች ከዜዋቄ በፊት በኤርምያስ የተነገሩ እንጂ የዘካርያስ አይደሉም ያሉ ሊቃውንት አሉ። ሌሎችም ደግሞ በምዕራፍ 9፣1-10፣12 በታላቁ እስክንድር ጊዜ የተደረገ የግሪካውያን ወረራ /322/ ነው። በምዕራፍ 13፣7-14፣21 ስለ ይጹ መቃቢስ ሞት /161/ የተዘጋጀ የማጽናኛ መዝሙር ነው በማለት እነዚህ ስድስት ምዕራፎች ባልታወቁ ነቢያት የተነገሩና የተጻፉ አድርገው ያስባሉ። ይሁን እንጂ ጸሐፊው ዘካርያስ ወይም ሌላ ነቢይ ቢሆን ቃሉ የአግዚአብሔር ነው ቃለ እግዚአብሔርነቱ አይፋለስም።

**የመጽሐፉ ዓላማ**

የትንቢተ ዘካርያስ ዋና ዓላማ "ወደ እኔ ተመለሱ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ። /1፣3/ የሚለው ነው። መጽሐፈ ዘካርያስ ሁለተኛውን ቤተ መቅደስ በመሥራት ላይ የነበሩ ሕዝቦቹን ያጽናናል አሕዛብ እንደሚወድቁ፣ ኢየሩሳሌምም እንደምትበለጽግ ይናገራል። ይህ መጻኢ በረከትም በመሢሑ በኩል የሚፈጸመው ነው። ዘካርያስ እንደ ኢሳይያስ ደረቅ ሐዲስ አለበት 6፣12-13። 9፣9።

**አከፋፈሉ**

ትንቢተ ዘካርያስ በአራት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል።

ሀ.ምዕራፍ 1፣1-6 የመጽሐፉ መቅድም። ነው

በዚህ ክፍል፡- ዘካርያስ ትንቢት መናገር የጀመረበት ዘመን፣ ዓመትና ወር ተገልጦአል። ነቢዩ በዚህ ክፍል ሕዝቡ በአባቶቻቸው መንገድ /የክፋት/ እንዳይሄዱ ግን ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ በቅድሚያ ያስጠነቅቃል።

ለ. ምዕራፍ 1፣7-6፣15 ስምንት ራእዮች

1. 1፣7-17 አንደኛው ራእይ በባርነት መካከል ቆሞ የታየው መልአክ፣ እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚፈጸመውን ድርጊት ሁሉ በመላእክት አማካኝነት ይመለከታል። በመጋላ /ቀይ/ ፈረስ ላይ የተቀመጠው ሰው መልአክ እግዚአብሔር ነው። በሰላማም ያሉት ባለፈረሶች ትእዛዙን ለመፈጸም በምድር ላይ የሚዞሩ የእግዚአብሔር የፍርድ መሣሪያዎች በምድር ሁሉ ላይ ፀጥታና ሰላም ሰፍኖ ስለ ኢየሩሳሌምና ይሁዳ ለምን እንደሚሠቃዩ በቁ.12 ላይ ለቀረበው ጥያቄ የዘካርያስ አስተርጓሚ መልአክ በቁጥር 13-17 ይመለስለታል። በአሕዛብ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይሆል፣ ኢየሩሳሌምና ቤተ መቅደሱ እንደገና ይገነባሉ።

2. 1፣18-21 ሁለተኛው ራእይ አራት ቀንዶችና አራት ጠራቢዎች አራቱ ቀንዶች አራቱ አጽራር መንግሥት እግዚአብሔር ናቸው። አራቱ ጠራቢዎችም አራቱን አጸራር የሚሰባበሩ አራቱ ሊቃ መላእክት ናቸው። አራቱ ቀንዶች ዳንኤል በራእዩ ያያቸውን አራቱን መንግሥታት ባቢሎንን፣ ፋርስና ሜዶንን፣ ግሪክንና ሮምን ያመለክታሉ። እነዚህን አሕዛብ በቀንድ መመሰልም ከዳንኤል 7፣7-8 ጋር ይመሰላሉ።

3. ምዕራፍ 2፣1-13 ሦስተኛው ራእይ መለኪያ ገመድ የያዘው ሰው። በጊዜው የነበረው የኢየሩሳሌም የቆዳ ስፋትና ርዝመት በቂ ሰፊና ረዥም ባይሆንም በኋላ ዘመን በእግዚአብሔር ትደግና የሚሆነውን ስፋትና ርዝመት ያመለክታል።

4. ምዕራፍ 3፣1-10 አራተኛው ራእይ፣ የታላቁ ካህን መክሰስና መንጻት። አያሱ እድፋም ልብስ ለብሶ ይታያል። ይህም የኀጢአት ምልክት ነው። እንደገና መልአኩ ንፁሕ ልብስ ማልበሱ የሥርየት ምሳሌ ነው። በአማርኛው እግዚአብሔር አለው አግዚአብሔር ይገሥጽሕ የተባለው በግእዙ ወይቤሎ መልአከ እግዚአብሔር ለይገሥጾከ እግዚአብሔር ተብሎአል። ምንም እንኳ በዕብራይስጡ እንደዚህ ባይልም መሠረተ ሀሳቡ አልአከ እግዚአብሔር ለማለት ስለሆነ ትክክለኛ ነው።

5. ምዕራፍ 4፣1-14 አምስተኛው ራእይ ተቅዋመ ወርቅና ሰብዓቱ መለትው፣ ለጊዜው ተቅዋመ ማሕቶት ሕዝበ እግዚአብሔር ናቸው። ሰብዓቱ መለትው ሰብዓቱ ሐበታት /ኢሳ.11፣2-5/። ሁለቱ የወይራ ዛፎች ሁለቱ ትብዓን መሪዎች ኢያሱና ዘሩባቤል ናቸው /ቁ.14/።

6. ምዕራፍ 5፣1-4 ስድስተኛው ራእይ፣ በራሪው የመጽሐፍ ጥቅልል፦ የመለኮታዊ ፍርድ ምልክት ነው። አማርኛው በራሬ መጽሐፉ የሚለውን ግእዙ "ማዕፀድ ዘይሠርር" ብሎታል። እርግጡ የአማረኛው ነው። በዕብራይስጡ ማግሎህ ይላልና። ሚግሎህ ማለትም የመጻሐፉ ጥቅልል ማለት ነው።

7. ምዕራፍ 5፣5-11 ሰባተኛው ራእይ በኢፍ መስፈሪያ የተቀመጠችው ሴት፣ የእስራኤል ኃጢአት መሰፈሩን ያሳያል ሰትዬዋም የኅጢአት መልክት /ቁ.8/ ናት ሕዝቡ አስታሮት የተባለችውን የአሕዛብ እንስት ጣኦት ያመልኩ እንደነበር ያመለክታል።

8. ምዕራፍ 6፣1-8 ስምንተኛው ራእይ አራቱ ሠረገላዎች፦ እነዚህ አራት ሠረገላዎች መለኮታዊ ፍረድ የሚፈጸምባቸው አራቱ ነፍሳት /ቁ.5/ ናቸው ወይም አራቱ ሊቃነ መላእክት ናቸው።

9. ምዕራፈ 6፣9-15 ስለ መሣሉ የተነገሩ ትንቢት በዚህ ክፍል ያለው ትንቢት ከኢሳይያስ 11፣1-5 እና ከኤርምያስ 33፣15-16 ጋር ተመሳሳይ ነው። በቁጥር 13 መሲሑ ንጉሥም ካህንም መሆኑን ያሳያል።

### ሐ. ምዕራፍ 7፣1-8፣23 ስለ ጾም የቀረበ ጥያቄ

በዚህ ክፍል የለው ቃል ተንቢት በዳርዬስ ቀዳማዊ 4ኛ ዓመት መንግሥት በ9ኛው ወር በአራተኛው ቀን ለዘካርያስ ተገልጦአል። ይኸውም የቤቴል ሰዎች ኢየሩሳሌምና ቤተመቅደሱ የፈረሱበትን ቀን እንደ ጾም ቀን አድርጐ ስለመጠበቅ ለቀረበው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነው። ሕዝቡ ቢታዘዙ በመንገዱም ቢሄዱ እግዚአብሔር ከተትረፈረፈ በረከቱ ጋር ወደ እነርሱ ይመለሳል።

ሠ. ምዕራፍ 9፣1፣14፣21 መጻእያት የዓለም ኃይላትና የእግዚአብሔር መንግሥት

1. 9፣1-10 ፣12 ጽዮን ነፃ ትወጣለች። በአረማዊው ዓለም ላይም ድል አድራጊ ትሆናለች። ይህም በመሢሐዊው ንጉሥዋ በኩል ይፈጽማል።
2. ምዕራፍ 11፣1-17 መልካምና ሰነፍ እረኛ
3. ምዕራፉ 12፣1-13 ፣6 የእስራኤል ወደ እግዚአብሔር መመለስ። የመሢሑ በጦር መወጋት በዚህ ክፍል ተነግሮአል /13፣10/
4. ምዕራፍ 13፣7፣14፣21 እስራኤልን ለማጥራት /ጥራት ያለው ሕዝብ ለማድረግ/ የሚሆን ፍርድና መጻእው የኢየሩሳሌም ክበር የመሢሑ መገደልና የተከታዮቹ መበተን በዚህ ክፍል ተገልጣአል /14፣7/

ትንቢተ ዘካርያስ በመጨረሻ ጊዜ የእግዚአብሔር መንግሥት በዓለም ሁሉ እንደሚሰበክ ዓለምም እንደምትለውጥ /14፣9-11/ እግዚአብሔርን የሚያውቁ ሁሉ የእግዚአብሔርን ሰዎች የልብስ ዘርፍ ይዘው /8፣93/ እግዚአብሔርን እንደሚፈልጉ ያስተምራል።

## ዘሚልክያስ

### ስሙ

ስሙ በዕብራይስጥ አጠራር ማላኪ ይባላል ትርጓሜውም መልእክቴ /መልእክተኛ ማለት ነው የኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንትም ሚልክያስ ማለት መልአክ ሐዋርያ ማለት ነው ብለው ይተረጉማሉ። ማልኪያስ የሚለው አጠራር የሰብዓ ሊቃውንት ነው። የግዕዙም መጽሐፍ ነው

ስለ ነቢዩ ሚልክያስ የምናውቀው ታሪክ የለም። በራሱ መጽሐፍም ሆነ በሌሎች የብሉይ ኪዳን ሊቃውንትም ሚልክያስ ማለት መልአክ ሐዋርያ ማለት ነው ብለው ይተረጉማሉ። ሚልክያስ የሚለው የጠራር የሰብዓ ሊቃውንት ነው። የግዕዙም መጽሐፍ ቅዱስ

ስለ ነቢዩ ሚልክያስ የምናውቀው ታሪክ የለም። በራሱ መጽሐፍም ሆነ በሌሎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስለ እርሱ የተጻፈ ነገር የለምና። ከዚህም የተነሣ ሚልክያስ ልዩ መጠሪያ ስም አይደለም፣ ሚልክያስ በመባል የታወቀም ነቢይ አልነበረም የሚሉ አንዳንድ ዘመናውያን ሊቃውንት አሉ። ለዚህም የሚከተለው ማስረጃ ያቀርባሉ።

1. በመጽሐፉ መግቢያ ላይ የነቢዩ ስም አልተጠሰም በአማርኛው መጽሐፈ ቅዱስ በሚልክያስ እጅ ለእሰራኤል የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ሸክም /1፣1/ ቢልም

በመሠረታዊው በዕብራይስጡ መጽሐፈ ቅዱስ በመልእክተኛየ እጅ ይላል። የሴፕቱአጊንታም አንጌሉ አፍቱ ይላል። የግእዙም ይህን በመከተል ተረፈ ቃለ እግዚአብሔር ዘኮነ ኀበ እስራኤል በአደ መልአኩ በማለት ያርቀዋል። እዚህ ላይ እንደምንመለከተው ከአማርኛው በቀር፡- ዕብራይስጡም ግሪኩም፣ ግእዙም ለነቢዩ ልዩ መጠሪያ ስም አልሰጡትም።

2. ለስሙ መግለጫ አልተሰጠም። ለምሳሌ ሚልክያስ ማላኪ/ ስመ ተጸውዖ ቢሆንም ኖሮየእገሌ ልጅ ወይም የዚህ ሀገር ሰው ተብሎ መገለጥ ነበረበት።
3. በትንቢተ ዘካርያስ 9፣1፣12፣1 "የእግዚአብሔር ቃል ሸክም" ብሎ የማጀምረው ዐረፍተ ነገር ባለቤት ለሌላው መጸሐፍ መታወቂያ ምልክት ነው። የሚልክያስም መጽሐፈ በዚሁ መጀመሩ ባለቤቱ አለመታወቁን ወይም ከሌላ የተወሰደ መሆኑን ያሳያል።
4. ዮናታን ቤንኤዚአል በተረጐመው በአራማይክ ብሉይ ኪዳን /ታርጉሞ/ ዕዝራ ጸሐፊ በተባለው በመልእክተኛዬ እጅ ለእስራኤል የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ሸክም ይላል። በዚህም ሀሳብ አባ ሄሮኒሞስ /ጀሮም/ ተስማምቶአል /ራሺ/ የተባለውም /104-105/ የዮናታንን ሀሳብ ደግፎአል። ስለዚህ ይህን የደቂቀ ነቢያት መጨረሻ የሆነውን መጽሐፈ የጻፈ ዕዝራ ጸሐፊ እንጂ ሚልክያስ /ማላኪ/ አይደለም ይላሉ።
5. በዚሁ መጽሐፍ 3፣1 ላይ "መልእክተኛዬን እልካለሁ" ይላል ይህም በምዕራፍ 1፣1 ላይ ማላኪ ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህ ቃል ልዩ መጠሪያ ስም ቢሆን ኖሮ ነቢዩ ሰለራሱ እንደዚህ /3፣1/ ሊናገር አይችልም ነበር።

ነገር ግን ብዙዎች የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት በዚህ አስተያየት አይስማሙም። የደቂቀ ነቢያትን መጨረሻ መጽሐፍ የጻፈ ሰው ስሙ በትክክል ማልክያስ /ማላኪ/ ነው፣ በማለት የሚከተለውን ማስረጃ ያቀርባሉ።

1. በብሉይ ኪዳን ውስጥ በዩድ የሚጨርስ /በአንደኛ መደብ በነጠላ ዘርዝር የማጨርስ /ስም የተለመደ ነው። ለምሳሌ አኔ /ስጦታየ/ 1ዜና. 6-41/ አቡ/ አባቶ/ 2ነገ.18 2/ሐጌ/ በዐልየ/ በዚህ መሠረት ማላኩ/ መልእክተኛዩ/ መጠሪያ ስም ሊሆን ይችላል።
2. እንደሌሎች ነቢያት የማን ልጅ ወይም የየት ሀገር ሰው መሆኑ በአለመገለጡ መላኪ/ ማልክያስ/ የነቢዩ መጠሪያ ስም ከመሆኑ ሊወጣ አይችልም። ይህም ከአብድዩ ጋር ተመሳሳይ ነው። አብድዩ የማን ልጅ የየት ሀገር ሰው መሆኑ አልተገለጠምና።
3. የትንቢት መጻሐፍት ሁሉ ባለቤት የለሽ /አኖኒሞስ/ አይደሉም። ስለዚህ ማላኪ የዚህ ትንቢት ተናጋሪና ጸሐፊ ነው።

4. ምንም እንኳን ምንጩ ባይታወቅም እንደ ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ትርጓሜ የሚልክያስ አባቱ ፋሄ እናቱ ኤድገኒ ይባላሉ። ትውልዱም ከነገደ ይሳኩር ነው። በዚህም ሚልክያስ /ማላኪ/ የውል ስም ሳይሆን የነቢዩ ልዩ መጠሪያ ስም መሆኑን እንረዳለን።

**ነቢዩ የነበረበት ዘመን**

ነቢዩሚልክያስ መቼ እንደነበረ በግን ዘመን እንደኖረ በመጽሐፉ ውስጥ አልተጠቀሰም ይሁን እንጂ ነህምያ ክፋርስ ባቢሎን ከመመለሱ በፊት በ460 ቅልክ ገደማ እንደነበረ ተገምቶአል። ይህም ግምት ከትንቢቶቹና ስለ ኢሩሳሌም ከሚናገሩት ሁኔታዎች ሊታወቅ ተችሎአል። ሕዝቡ በፋርሳዊ ገዥ /አለቃ/ ይገዙ ነበር። የሁለተኛው ቤተ መቅደስ ሥራ ተፈጽሞ በጥቅም ላይ ውሎ ነበር /ሚል.1፣8፣3፣1፣10/። ነህምያ የኢየሩሳሌም አስተዳዳሪ በሆነ ጊዜ የገጠመው ተግር ሁሉ ሚልክያስን ገጠሞታል። ነህምያ ቅልቅል ጋብቻን እንደተቃወመ ማልክያስም ተቃውሞአል። ሚል. 2፣10.12። ነህ.13፣23-27 ነህምያ የአይሁድን የአምልኮት ግድየለሽነት ተቃውሞአል። እንደዚሁም የሚክያስ በዚህ ላይ ተቃውሞአል። እንደዚሁም ሚልክያስ በዚህ ላይ ተቃውሞ አድርጓአል። /ሚል.1፣6-8። 3፣7-10 ነህ.10፣1-39/ ሁለቱንም ሰዎች በይሁዳ ተመሳሳይ ችግር ገጥሞአቸዋል። ሁለቱም ችግሩን ለማስወገድ ተመሳሳይ ጥረት አድርገዋል።

ስለዚህ ሚልክያስ ከነህምያ ቀደም ብሎ የነቢይነት አገልግሎትን እንደጀመረ እንደተጠቀሱ እርሱም ከነህምያ ጋር ይጠቀስ ነበር። ከነህምያም በጎላ የተነሣ ቢሆን ኖሮ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ሁሉ በነህምያ ጊዜ ተወግደው ነበርና ሚለክያስ ደግሞ ባላነሣቸው ነበር። በዚህ መሠረት ነህምያ በኢየሩሳሌም አስተዳዳሪ የነበረበት ዘመን 444 ቅልክ ሲሆን ሚልክያስ ደግሞ ከዚህ በፊት በ460 ቅልክ እንደነበረ በብዙዎች የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ዘንድ ታምኖበታል።

**መጽሐፉ**

1. አቀማመጡ፡- በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ፡- ትንቢተ ሚልክያስ ጽሑፎች ከተባሉት በፊት የነቢያት መጨረሻ ነው። በሰብዓ ሊቃናት ግን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ መጨረሻ ነው። ከዚህም የተነሣ በማንኛውም ቋንቋ የተተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ትንቢተ ሚልክያስን የብሉይ ኪዳን መጻሐፍት መደምደሚያ አድርጎት ይገኛል።

2. ምዕራፉ፡- ትንቢተ ሚልክያስ፡- በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ 3 ምዕራፎች ብቻ አሉት። በእሃ መጽሐፈ ቅድስ ምዕ.4፣1-6 የሆነው በዕብራይስጡ ምዕ.3፣19-24 ነው። በአራት ምዕራፍ አድርገው የከፈሉት ግን ሰብዓ ሊቃናት ናቸው።
3. ንባቡ፡- የዕበራይስጡ፣ የግእዙና የአማርኛው መጽሐፈ ቅዱስ የትንቢተ ማልክያስ ንባብ እንዳንድ ልዩነት ያሳያል። ለምሳሌ፡- ዕብራይስጡ በመልእክተኛዬ እጅ ለእሰራኤል የሆነ የእግዚአብሔር ቃል" ሲል በግእዙ "በእደ መልአኩ" ይላል። /1፣1/። ምዕራፍ 3፣1 ላይ "እናንተ የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል" ይላል ዕብራይስጡ ግእዙ ግን ውስተ ጽርሑ ይላል። ሌላም ልዩነት አለ።

## አከፋፈሉ

ትንቢተ ሚልክያስ በ2 ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል።

1. ምዕራፍ 1፣1-3፣15በጥየቄና መልስ የቀረበ መልእክት

በዚህ ክፍል ዘጠኝ ጥያቄዎች ከሕዝቡ ቀርበዋል፣ ነቢዩም ለጥያቄዎቹ ሁሉ መልስ ሰጥቶአል።

1. ምዕራፍ 1፣1-5 አንደኛው ጥያቄ ፣ ሕዝቡ እግዚአብሔርን በምን ወደድኸን? ብለውታል።
2. ምዕ.1፣6 ሁለተኛው ጥቄ ስምህን በምን አቃለልን?
3. ምዕ.1፣7፣2:9 ሦስተኛው ጥያቄ ያረከስንህ በምንድን ነው?
4. ምዕ.2፣10፣16 አራተኛው ጥያቄ ቁርባናችንን የማትቀበለው ስለምንድን ነው?
5. ምዕ.2፣17 አምስተኛው ጥያቄ እግዚአብሔርን የታከትነው በምንድን ነው?
6. ምዕ.2፣17፣3፣5 ስድስተኛው ጥያቄ የፍርድ አምላክ ወደት አለ?
7. ምዕ.3፣6-7 ሰባተኛው ጥያቄ። የምንመልሰው በመንድን ነው?
8. ምዕ.3፣12 ስምንተኛው ጥያቄ የሠረቅንህ በመንድን ነው?
9. ምዕራፍ 3፣13-15 ዘጠነኛው ጥያቄ

በአንተ ላይ ደፍረን የተናገርነው በምንድን ነው?

2. ምዕራፈ 3፣16-4፣5 እግዚአብሔርን የሚፈሩ በፍርድ ቀን ተጠብቀው ይኖራሉ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቀን ሳይደርስ እንዲመለሱ ተጠርተዋል። በዚህ ክፍል ነቢዩ ሚልክያስ የአይሁድን ትውፊት ተከትሎ ይናገራል። ይህም ትውፊት በመጨረሻ ጊዜ ወይም

በዕለቱ እግዚአብሔር "ኤልያስ ይመጣል" የሚለው ነው። ነገር ግን ኤልያስ ይመጣል የማለውን ተንቢት ጌታችን ኢየሱስ ለዮሐንስ ሰጥቶ ተርጉሞታለ /ማቴ.17፣11-12/። ይሁን እንጂ በአይሁድ ዘንድ አሁንም "ኤልያስ ይመጣል" የሚለው ትንቢት ገና ፍጻሜን አንዳላገኘ ሆኖ ይጠበቃል። ከዚህም የተነሣ አንድ ሃይማኖታዊ ተግር ሲገጥማቸው "ኤልያስ ሲመጣ ይፈታዋል" የሚል የተለመደ አነጋገር አላቸው። ለምሳሌ ነቢዩ ሕዝቅኤል ስለ ሥርዐተ መስዋዕት የተናገረው ቃል ሁሉ ሙሴ ከጻፈው ሥርዐተ መሥዋዕት ጋር አይስማማም። በዚህም ምክንያት መጽሐፈ ሕዝቅኤል ከቀኖናውያን መጻሐፈት እንዳይቆጠር ክርክር ነበር። ግን ከረበናት አንዱ ዮናታን፡- በኦሪተ ሙሴና በመጽሐፈ ሕዝቅኤል መካከል ያለውን ችግር ኤልያስ ሲመጣ ይፈታዋል በማለት ተቀብለውታል። ዮሐንስም በራእዩ የኤልያስን መምጣት በራእዩ ጽፎአል /ራእ.11፣4፣10/።